# የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የ2005 የባጀት አመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት

ሐምሌ 2005
ዓዲግራት

**ይዘት** **ገፅ**

1. መግቢያ .......... 3
2. መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ .......... 3
2.1 ተማሪዎችና ትምህርት ክፍሎች .......... 3
2.2 የአካዳሚክ ሰራተኞች .......... 7
2.3 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች .......... 9
2.4 የተመደበልን ባጀትና አጠቃቀሙ .......... 11
2.5. የግንባታ ሰራዎች አፈፃፀም 17
3 የእቅድ ኣፈፃፀም .......... 21
4 ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች 40

## 1. መግቢያ

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ግንቦት 18/2003ዓም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 223/2003 **"ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ"** በሚል የተቋቋመ መንግስታዊ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲሆን ተጠሪነቱም ለትምህርት ሚኒስቴር ነው። ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን በ2004ዓም የትምህርት ዘመን ትምህርት ከጀመሩት ዘጠኝ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን አንዱ ሆኖ በ2005 የትምህርት ዘመን በአጠቃላይ በአንደኛ ሰሚስተር ከአራት ሺ ተማሪዎች በላይ በሁለተኛ ሰሚስተር ደግሞ ከሶስት ሺ አምስት መቶ በላይ ተማሪዎችን ይዞ የአመቱ ተግባራቱን አጠናቋል።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እንደሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ሶስት ዋና ዋና ተልእኮዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ማስተማር፤ ምርምር እና የህብረተሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማከናወን ናቸው። ዩኒቨርሲቲያችን እነዚህን ተልእኮዎች በኣጥጋቢ መልኩ ለማሳካት ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ዓመታዊ እቅዱን ካዘጋጀ በኋላ እነሆ በባጀት አመቱ (ማላትም ከሃምሌ 1፣ 2004ዓም እስከ ሰኔ 30፣ 2005ዓም)ያከናወናቸው ተግባራት የሚያሳይ ሪፖርት አቅርበናል።

ዩኒቨርሲቲው የ2005 ስራውን የጀመረው ሰኔ 30፣ 2004 ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ምምህራንና ሰራተኞች በተገኙበት ያለፈውን ዓመት የስራ አፈፃፀም ዓመታዊ ግምገማ በማድረግ ነው። በዚህ መድረክ ዩኒቨርሲቲው በአጠቃላይ እና የተለያዩ ክፍሎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉት የአመራር አካላት የነበራቸውን ጠንካራ ጎኖችና ውስንነቶች በአግባቡ በመለየት፤ ጥንካሬዎች በበለጠ ተጠናክረውና ሁሉም የራሱ አድርጎ እንዲወስዳቸው በሚያስችል መልኩ ድክመቶችን ደግሞ ለቀጣይ በሚፈፅማቸው ኣካል ብቻ ሳይሆን በሁሉም የዩኒቨርሲቲው ኣካላት በማይደገሙበት መልኩ ትምህርት እንዲወሰድባቸው በሚያስችል መልኩ ግምገማችን አካሂደን የ2005ዓም ስራችን ጀምረናል።

በዚህ መሰረት በየዘርፉ የተለያዩ ስራዎች ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን በመማር ማሰተማር ዘርፉ በኩል በመጀመሪያ በሃምሌና በነሃሴ ወራት የዓመቱን ትምህርት የማጠናቀቅ (በ2004ዓም ት/ት የተጀመረው ታህሳስ ወር ስለ ነበር የዓመቱን ትምህርት እሰከ ነሃሴ ኢጋማሽ መቆየት ነበረበት) ስራ የተከናወነ ሲሆን ጎን ለጎንም ሁሉም የመንግሰት ዩኒቨርሲቲዎች እንዲከተሉት የተወሰነው የሞጁላራይዜሽን ስራ በመጀመር ነበር። ሞዱላር አካሄድ የመጠቀም ስራ አመቱን ሙሉ ትኩረት ተሰጥቶት በየደረጃው ያሉት የአመራር አካላት እና መምህራን በስፋት ባሳተፈ መልኩ ሲሰራበት የከረመ ተግባር ነበር።

## 2. መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ

### 2.1 ተማሪዎችና ትምህርት ክፍሎች

ዩኒቨርሲቲው በ2005 የትምህርት ዘመን በ2004 የገቡት የሁለተኛ አመት ተማሪዎችና በ2005 የተመደቡለትን አዲስ ተማሪዎችን በመቀበል ነው ስራውን ያከናወነው። በ2005 የተመደቡት አዲስ ተማሪዎች (Freshman Students) በስድስት ባንዶች ወይም ኮሌጆች ሲሆን እነሱም ባንድ 1 (ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ)፤ ባንድ 2 (የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ)፤ ባንድ 3 (ህክምናና ጤና ሳይንስ)፤ ባንድ 4 (ግብርና)፤ ባንድ 5 (ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ) እና ባንድ 6 (ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ) ናቸው። ለ2005 እንቀበላቸዋለን ብለን በእቅድ የያዝናቸውና ለትምህርት ሚኒስቴር ያስታወቅነው የአዲስ ተማሪዎች ብዛት 3260 የነበረ ሲሆን በዚሁም መሰረት 3141 አዲስ የአገር ውስጥ ተማሪዎች እንዲሁም 117 ከኤርትራውያን ስደተኞች ተማሪዎች በድምሩ 3258 ተማሪዎች በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተመድበውልን የአመቱን ስራ አከናውነናል። ቀደም ብሎ በወጣው እቅድ መሰረት 2004 ክረምት ላይ አስፈላጊው ዝግጅቶች እየተደረጉ በመቆየታቸውና 48 ብሎኮችን የያዘው የመጀርያው ዙር ግንባታ በወሳኝ መልኩ የተጠናቀቀ ስለነበረ የተጠቀሱት ተማሪዎች ለመቀበል አስችሎናል። በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡልን የአገር ውስጥ ተማሪዎች በመጡበት ክልል እና ባገኙት የመሰናዶ ፈተና ውጤት ሲተነተን የሚከተለውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 1. የተመደቡልን ተማሪዎች በመጡበት ክልል

| ክልል/የከተማ አስተዳደር | ቁጥር | መቶኛ |
|---|---|---|
| ትግራይ | 1484 | 47.25 |
| ኦሮሚያ | 428 | 13.63 |
| አማራ | 420 | 13.37 |
| አዲስ አበባ | 313 | 9.96 |
| ደቡብ ህዝቦች | 281 | 8.95 |
| ሶማሊ | 87 | 2.77 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 57 | 1.81 |
| ዓፋር | 23 | 0.73 |
| ጋምቤላ | 21 | 0.67 |
| ድሬዳዋ | 13 | 0.41 |
| ሃረሪ | 7 | 0.22 |
| ሌሎች አገሮች | 7 | 0.22 |
| ድምር | 3141 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ 1 እንደተቀመጠው ወደ ዩኒቨርሲቲው የተመደቡ ተማሪዎች ከሁሉም ክልል የተመደቡ ሲሆን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከትግራይ ክልል የተመደቡ ናቸው። ከትግራይ ቀጥሎ በተማሪዎች ብዛት በቅደም ተከተላቸው ከኦሮሚያ ከአማራ ከአዲስ አበባ እና ከደቡብ ህዝቦች የተመደቡት ይገኙበታል። የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤታቸውን በተመለከተ ደግሞ አብዛኛዎቹ ከ300 በታች ያገኙ ቢሆንም አምና ከተመደቡልን ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር የዘንድሮው ስርጭት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

ሰንጠረዥ 2. የተመደቡልን ተማሪዎች ባገኙት የፈተና ውጤት

| የተማሪዎች ውጤት (ከ700) | ብዛት |
|---|---|
| >=500 | 2 |
| >=400 | 205 |
| >=350 | 211 |
| >=300 | 1660 |
| >=290 | 838 |
| >=268 | 225 |
| | 3141 |

ኢ.ዲስ ተማሪዎችን ከተቀበልን በኋላ የትምህርት ክፍል መረጣና ምደባ የተደረገ ሲሆን ምደባው ተደርጎ ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩ የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት (የአንደኛ አመት እና የሁለተኛ አመት መደበኛ ተማሪዎች) 3842 ነው። ወደ ዩኒቨርሲቲው ከተመደቡት 3258 አዲስ ተማሪዎች ውስጥ ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩት 3074 (95%) ሲሆኑ የተቀሩት ተማሪዎች ሪፖርት አላደረጉም።

በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩት መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 3842 የነበረ ሲሆን በሁለተኛ ሰሚስተር የመበሩን የመደበኛ ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ ወደ 3504 ቀንሶ ተገኝቷል። በየኮሌጁና በየትምህርት ክፍሉ ያለው የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት በሰንጠረዥ 3 የተቀመጠውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 3. በ2005 በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ የሁለተኛ ሰሚስተር መደበኛ ተማሪዎች

| College | Department | First Year | | | Second Year | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | Total |
| Engineering and Technology (Band I) | Preengineering | **755** | **387** | **1142** | | | | **755** | **387** | **1142** |
| | Civil Engineering | | | **0** | 63 | 100 | 163 | **63** | **100** | **163** |
| | Computer Science | 29 | 25 | **54** | | | 0 | **29** | **25** | **54** |
| | Electrical Engineering | | | **0** | 28 | 25 | 53 | **28** | **25** | **53** |
| | Chemical Engineering | | | **0** | 27 | 26 | 53 | **27** | **26** | **53** |
| | Mechanical Engineering | | | **0** | 40 | 14 | 54 | **40** | **14** | **54** |
| | **Sub Total** | **784** | **412** | **1196** | **158** | **165** | 323 | **942** | **577** | **1519** |
| Natural and Computational Sciences (Band II) | Biology | 48 | 77 | **125** | 13 | 61 | 74 | **61** | **138** | **199** |
| | Chemistry | 45 | 51 | **96** | 8 | 60 | 68 | **53** | **111** | **164** |
| | Mathematics | 52 | 25 | **77** | 11 | 31 | 42 | **63** | **56** | **119** |
| | Physics | 55 | 28 | **83** | 4 | 22 | 26 | **59** | **50** | **109** |
| | Statistics | 42 | 11 | **53** | | | 0 | **42** | **11** | **53** |
| | Geology | 26 | 27 | **53** | | | 0 | **26** | **27** | **53** |
| | Sport Science | 29 | 20 | **49** | | | 0 | **29** | **20** | **49** |
| | **Sub Total** | **297** | **239** | **536** | **36** | **174** | 210 | **333** | **413** | **746** |
| Medical and Health Sciences (Band III) | Medicine | 40 | 13 | **53** | | | 0 | **40** | **13** | **53** |
| | Nursing | 16 | 16 | **32** | | | 0 | **16** | **16** | **32** |
| | Midwifery | 21 | 5 | **26** | | | 0 | **21** | **5** | **26** |
| | Health Officer | 32 | 13 | **45** | | | 0 | **32** | **13** | **45** |
| | **Subtotal** | **109** | **47** | **156** | | | 0 | **109** | **47** | **156** |
| Agriculture and Environmental Science (Band IV) | Plan Science, Crop Production | 26 | 13 | **39** | | | 0 | **26** | **13** | **39** |
| | Animal and wildlife Science | 33 | 3 | **36** | | | 0 | **33** | **3** | **36** |
| | Natural Resource Management | 18 | 23 | **41** | | | 0 | **18** | **23** | **41** |
| | **Subtotal** | **77** | **39** | **116** | | | 0 | **77** | **39** | **116** |
| Business and Economics (Band V) | Accounting and Finance | 127 | 68 | **195** | 23 | 38 | 61 | **150** | **106** | **256** |
| | Economics | 99 | 9 | **108** | 26 | 14 | 40 | **125** | **23** | **148** |
| | Management | 97 | 71 | **168** | 26 | 30 | 56 | **123** | **101** | **224** |
| | **Sub Total** | **323** | **148** | **471** | **75** | **82** | 157 | **398** | **230** | **628** |
| Social Sciences and Humanities (Band VI) | English Language and Literature | 32 | 33 | **65** | 8 | 27 | 35 | **40** | **60** | **100** |
| | Civics and Ethical Education | 34 | 32 | **66** | 19 | 24 | 43 | **53** | **56** | **109** |
| | Psychology | 43 | 20 | **63** | | | 0 | **43** | **20** | **63** |
| | Geography and Environmental Science | 32 | 35 | **67** | | | 0 | **32** | **35** | **67** |
| | **Subtotal** | **141** | **120** | **261** | **27** | **51** | 78 | **168** | **171** | **339** |
| **Overall Total** | | **1731** | **1005** | **2736** | **296** | **472** | **768** | **2027** | **1477** | **3504** |

የፆታ ሰብጥርን በተመለከተ ከአጠቃላይ መደበኛ ተማሪዎች 2027 (58%) ወንዶች ሲሆኑ 1477 (42%) ሴቶች ናቸው። የ70፤ 30 ስርጭት በተመለከተ ደግሞ በየባንዱ የሚከተለውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 4. የ70፤30 ስርጭት (መደበኛ ተማሪዎች)

| ባንድ | ወ | ሴ | ድ | ፐርሰንት | 70፡30 ቀመር |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ (ባንድ 1) | 942 | 577 | 1519 | 0.43 | |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ (ባንድ 2) | 333 | 413 | 746 | 0.21 | |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ (ባንድ 3) | 109 | 47 | 156 | 0.04 | |
| ግብርና (ባንድ 3) | 77 | 39 | 116 | 0.03 | 0.72 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ (ባንድ 5) | 398 | 230 | 628 | 0.18 | |
| ህብረተሰብ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ (ባንድ 6) | 168 | 171 | 339 | 0.10 | 0.28 |
| ድምር | 2027 | 1477 | 3504 | 1 | |
| ፐርሰንት | 0.58 | 0.42 | 1 | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 4 እንደተቀመጠው በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲሟላ የሚፈለገው ከተማሪዎቹ 70% በተፈጥሮ ሳይንስ መስኮች (ባንድ 1፡ 2፡ 3 እና 4) ሲሆን የተቀሩት 30% ደግሞ በማህበራዎ ሳይንስ መስኮች (ማለትም ባንድ 5 እና 6) ነው። በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የመደበኛ ተማሪዎች ስብጥር 72% ያህሉ በተፈጥሮ ሳይንስ እና 28% ያህሉ ደግሞ በማህበራዎ ሳይንስ በሚገኙ ትምህርት ክፍሎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በተፈጥሮ ሳይንስ መስኮች ያሉት ተማሪዎች ብዛት በአገር አቀፍ ከሚፈለገው ቀመር በላይ የሆኑ ቢሆንም ቀመሩ በአቀር አቀፍ ደረጃ የሚሰላ በመሆኑ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጉድለቶች ካሉ ያንን ጉድለት ለማሟላት የራሱን አስተዋፅኦ ይኖረዋል ማለት ነው። የየባንዱ ስርጭት ሲታይ ደግሞ አብዛኛዎቹ (43%) ተማሪዎቻችን በኢንጂነሪንግ መስክ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። ይህም ማለት በዚህ መስክ መኖር ከሚገባቸው (ማለትም 40%) በላይ መሆኑን ያመለክታል።

ከተመደቡልን 117 ኤርትራውያን ስደተኞች ውስጥ 94 በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው በትምህርት ላይ የነበሩ ሲሆን ሌሎቹ ግን ወደ ዩኒቨርሲቲው ሪፖርት አላደረጉም። በሁለተኛ ሰሚስተር ትምህርት ላይ ያሉት የኤርትራ ተማሪዎቹ ቁጥር ለብቻ ያልተሰላ ሲሆን ተማሪዎቹ የተመደቡት በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ፤ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስና በማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ በሚገኙ ትምህርት ክፍሎች ነው።

በአንደኛ ሰሚስተር ትምህርት ላይ ከነበሩት ተማሪዎች ውስጥ (ማለትም 3854) በሚከተለው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በርከት ያሉ ተማሪዎች ትምህርት አቋርጠዋል። ተቀባይነት ባለው ምክንያት አስፈላጊ ፎርማሊቲዎችን አሟልተው ትምህርት ያቋረጡ (withdrawals) ተማሪዎች ብዛት 39 ወይም 1% ሲሆኑ በራሳቸው ምክንያት አስፈላቲ ፎርማሊቲዎችን ሳያሟሉ ትምህርት ያቋረጡ (dropouts) ደግሞ 161 ወይም 4.18% ናቸው። በአንደኛ ሰሚስተር መጨረሻ ላይ በትምህርት ድክመት ምክንያት ትምህርት ያቋረጡት (dismissals) ተማሪዎች ብዛት 127 ወይም የጠቅላላው ተማሪዎች 3.3 ያህሉ ናቸው። በትምህርት ድክመት ያቋረጡ ተማሪዎች የሰሚስተር ውጤታቸው በዩኒቨርሲቲው ሰኔት ከታየ በኋላ የድህረ ማጠናከሪያ ትምህርት (post remedial) ተሰጥቶዋቸው እንደገና እንዲፈተኑ ተደርገው ወጤታቸውን ያሻሻሉት አይጨምርም። የድህረ ማጠናከሪያ ድጋፍ ከተሰጣቸው በኋላ ብዙ ተማሪዎች ውጤታቸውን ያሻሻሉ መሆናቸው ግምት ውስጥ በማስገባት በአጠቃላይ በሰሚስተሩ 327 ተማሪዎች ወይም ከጠቅላላው ተማሪዎች ቁጥር 8.48% በተለያየ ምክንያት ትምህርታቸውን ሊያቋርጡ ችለዋል። ዝርዝሩ በሚከተለው ሰነጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 5፤ በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች

| ባንድ | አንድኛ አመት | | | ሁለተኛ አመት | | | ጠቅላላ ድምር | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | |
| ዊዝድረዋል | 24 | 11 | 35 | 2 | 2 | 4 | 39 | 1.01 |
| ድሮፕ አውት | 85 | 65 | 150 | 2 | 9 | 11 | 161 | 4.18 |
| በትምህርት ድክመት | 41 | 55 | 96 | 7 | 24 | 31 | 127 | 3.30 |
| ድምር | 150 | 131 | 281 | 11 | 35 | 46 | 327 | 8.48 |

ከመደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው የተከታታይ ትምህርት በማታው ክፍለ ጊዜ የጀመረ ሲሆን በዚሁ ፕሮግራም የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ደግሞ 295 ነው። በየትምህርት ክፍሉ ያለው ስርጭት ደግሞ በሲቪል ምህንድስና 131 (120 ወንድ እና 11 ሴት)፤ ማኔጅመንት 32 (16 ወንድ 16 ሴት)፤ አካውንቲንግና ፋይናንስ 68 (42 ወንድ እና 26 ሴት) እና በነርሲንግ 64 (33 ወንድ እና 31 ሴት) ነው። ስለዚህ የመደበኛ እና የተከታታይ ትምህርት በአንድ ላይ ሲጠቃለል በሁለተኛው ሰሚስተር በዩኒቨርሲቲው በትምህርት ላይ ያሉት ተማሪዎች ብዛት 3799 ነው።

## 2.2 የአካዳሚክ ሰራተኞች

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ወቅት በድምሩ 252 መምህራን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 214 በስራ ላይ የሚገኙ የአገር ውስጥ መምህራን ሲሆኑ 12 ደግሞ በስራ ላይ ያሉ የህንድ መምህራን ናቸው። 26 ያህል የዩኒቨርሲቲው መምህራን ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪያቸው በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። ዩኒቨርሲቲው ካሉት የአካዳሚክ ሰራተኞች ውስጥ 17 (6.1%) የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ፤ 66 (26.4%) የመጀመርያ ዲግሪ ያላቸው ደጋፊ መምህራን፤ 160 (64.2%) የሚሆኑት ደግሞ በሌክቸረር መአርግ የሚገኙ መምህራን፤ እና የተቀሩት 8 (3.3%) አሲስታንትና አሶሴት ፕሮፌሰር መአርግ ያላቸው ናቸው። የፆታ ስብጥር በተመለከተ ደግሞ ከጠቅላላው መምህራን 19 (8.1%) ሴት መምህራን ናቸው።

ሰንጠረዥ 6፤ የአካዳሚክ ሰራተኞች

| ኪሌጅ | TAs | | | BA/BSc | | | MA/MSc/MD | | | ረ/ተ/ፕሮፌሰር | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ኢንጂነሪንግ | 8 | 2 | 10 | 20 | 2 | 22 | 25 | 2 | 27 | | | | 53 | 6 | 59 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 5 | | 5 | 7 | 1 | 8 | 56 | | 56 | 1 | | | 69 | 1 | 70 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | | | 0 | 8 | | 8 | 7 | | 7 | 2 | 2 | 4 | 17 | 2 | 19 |
| ግብርና እና አከባቢያዊ ሳይንስ | 2 | | 2 | | | 0 | 12 | 1 | 13 | 1 | | | 15 | 1 | 16 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | | 0 | 7 | 4 | 11 | 16 | 1 | 17 | 3 | | 3 | 26 | 5 | 31 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | | | 0 | 16 | 1 | 17 | 37 | 3 | 40 | | | | 53 | 4 | 57 |
| ድምር | 15 | 2 | 17 | 58 | 8 | 66 | 153 | 7 | 160 | 7 | 2 | 8 | 233 | 19 | 252 |
| % | | | 6.1 | | | 26.4 | | | 64.2 | | | 3.3 | 91.9 | 8.1 | 100 |

በስራ ላይ የሚገኙ የአገር ውስጥ መምህራን በየትምህርት ክፍሉ ያለው ስርጭት በሰንጠረዥ 7 ተመልክቷል።

## ሰንጠረዥ 7፤ በስራ ላይ ያሉ የአገር ውስጥ መምህራን ብዛት

| College | Department | Technical Assistants | | | BA/BSC (Assts.) | | | MA/MSc (Lect.) | | | PhD | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | Total | M | M | F | T |
| Engineering | Electrical Engineering | 2 | | 2 | 2 | | 2 | 3 | 1 | 4 | | 7 | 1 | 8 |
| | Mechanical Engineering | 2 | 1 | 3 | | | | 7 | | 7 | | 9 | 1 | 10 |
| | Chemical Engineering | | | | | | | 5 | | 5 | | 5 | 0 | 5 |
| | Civil Engineering | 3 | 1 | 4 | 7 | | 7 | 6 | 1 | 7 | | 16 | 2 | 18 |
| | Computer Science | 1 | | 1 | 8 | 1 | 9 | 1 | | 1 | | 10 | 1 | 11 |
| | **Sub Total** | **8** | **2** | **10** | **17** | **1** | **18** | **22** | **2** | **24** | **0** | **47** | **5** | **52** |
| Natural and Computational Sciences | Biology | 3 | | 3 | | | | 9 | | 9 | | 12 | 0 | 12 |
| | Chemistry | 1 | | 1 | | | | 12 | | 12 | | 13 | 0 | 13 |
| | Mathematics | | | | | | | 21 | | 21 | | 21 | 0 | 21 |
| | Physics | 1 | | 1 | | | | 8 | | 8 | 1 | 10 | 0 | 10 |
| | Statistics | | | | 2 | | 2 | | | | | 2 | 0 | 2 |
| | Geology | | | | | | | 2 | | 2 | | 2 | 0 | 2 |
| | Sport Science | | | | | | | 3 | | 3 | | 3 | 0 | 3 |
| | **Sub Total** | **5** | **0** | **5** | **2** | **0** | **2** | **55** | **0** | **55** | **1** | **63** | **0** | **63** |
| Business and Economics | Accounting and Finance | | | | | | | 4 | | 4 | | 4 | 0 | 4 |
| | Economics | | | | | 1 | 1 | 8 | | 8 | 1 | 9 | 1 | 10 |
| | Management | | | | | | | 4 | | 4 | | 4 | 0 | 4 |
| | **Sub Total** | **0** | **0** | **0** | **0** | **1** | **1** | **16** | **0** | **16** | **1** | **17** | **1** | **18** |
| Social Sciences and Humanities | English | | | | | | | 21 | 1 | 21 | | 21 | 1 | 22 |
| | Civics | | | | 10 | 1 | 11 | 7 | 2 | 9 | | 17 | 3 | 20 |
| | Psychology | | | | 2 | | 2 | 4 | | 4 | | 6 | 0 | 6 |
| | Geography and Environmental Stdies | | | | | | | 5 | | 5 | | 5 | 0 | 5 |
| | **Subtotal** | **0** | **0** | **0** | **12** | **1** | **13** | **37** | **3** | **39** | **0** | **49** | **4** | **53** |
| Agriculture and Environmental Science | Natural Resource Management (SWC) | | | | | | | 4 | | 4 | 1 | 5 | 0 | 5 |
| | Animal Science | 2 | | 2 | | | | 5 | | 5 | | 7 | 0 | 7 |
| | Plant Science | | | | | | | 3 | 1 | 4 | | 3 | 1 | 4 |
| | **Subtotal** | **2** | **0** | **2** | **0** | **0** | **0** | **12** | **1** | **13** | **1** | **15** | **1** | **16** |
| Health and Meidical Sciences | Nursing | | | | 3 | | 3 | | | | | 3 | 0 | 3 |
| | Midwifery | | | | 5 | | 5 | | | | | 5 | 0 | 5 |
| | Health Officer | | | | | | | | | | | 0 | 0 | 0 |
| | Medicine | | | | | | | 4 | | 4 | | 4 | 0 | 4 |
| | **Subtotal** | **0** | **0** | **0** | **8** | **0** | **8** | **4** | **0** | **4** | **0** | **12** | **0** | **12** |
| **Overall Total** | | **15** | **2** | **17** | **39** | **3** | **42** | **146** | **6** | **151** | **3** | **203** | **11** | **214** |

ከአገር ውስጥ መምህራን በተጨማሪ 12 ህንዳውያን መምህራን በማስተማር ላይ ይገኛሉ። በየትምህርት ክፍሉ ያሉት የህንድ መምህራን ብዛት በሚከተለው ሰንጠርዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 8. የህንድ መምህራን

| ትምህርት ክፍል | ብዛት | መአርግ |
|---|---|---|
| ኤሌክትሪካል ምህንድስና | 1 | ሌክቸረር |
| ኮምፕዩተር ሳይንስ | 1 | ሌክቸረር |
| ሲቪል ምህንድስና | 1 | ሌክቸረር |
| ስታቲስቲክስ | 1 | ሌክቸረር |
| አካውንቲንግና ፋይናንስ | 2 | ሌክቸረር፤ አሲስታንት ፕሮፌሰር |
| ማኔጅመንት | 1 | አሲስታንት ፕሮፌሰር |
| ነርሲንግ | 1 | ሌክቸረር |
| ህክምና | 4 | አሲስታንት ፕሮፌሰር |

ዩኒቨርሲቲው በ2005 27 መምህራንን ወደ ትምህርት የላከ ሲሆን አንድ ወደ ትምህርት የተላከች መምህር በፈቃድዋ ስራ አቋርጣለች። ትምህርት ላይ ያሉት በሙሉ ለሁለተኛ ዲግሪ በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን 12 የሚሆኑት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 7 በመቐለ ዩኒቨርሲቲ፤ 3 አዳማ ዩኒቨርሲቲ፤ 2 ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፤ 1 ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና 1 ደግሞ ውጭ አገር ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

**2.3 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች**

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ስራውን በጀመረበት የ2004 የትምህርት ዘመን በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተዘጋጅቶ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በኩል ተፈቅዶ የነበረው መዋቅር 380 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለመቅጠር የሚያስችለው ነበር። ሆኖም ይህ መዋቅር ዩኒቨርሲቲው ለማድረግ ካቀደው የመስፋፋት ስራ ጋር በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ አዲስ መዋቅር በማዘጋጀትና በሲቪል ሰርቪሰ ሚኒስቴር በኩል በማስፀደቅ ለነባር ሰራተኞች በአዲሱ መዋቅር መሰረት የቦታ ድልድል የተፈፀመ ሲሆን ተጨማሪ ቅጥሮችን ደግሞ በማካሄድ ላይ እንገኛለን። በአዲሱ መዋቅር መሰረት ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለት አጠቃላይ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 1186 ቢሆንም መዋቅሩ ለሶስት አመታት ያህል ሊያሰራን ይችላል በሚል እሳቤ የተዘጋጀ ስለሆነ ሁሉም ሰራተኞች በአንድ አመት ብቻ የሚቀጠሩ አይሆኑም። በፅዳት ስራን በተመለከተ ወደ ውጭ ለማውጣት (outsource) በተያዘው እቅድ መሰረት በሁለተኛው አጋማሽ የተፈፀመ ስለሆነ በከተማው ትምህርት ጨርሰው ለተደራጁት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋም እንዲሰጥ ተደርጓል።

ዩኒቨርሲቲው እስከ ሰኔ 30 ድረስ የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረገች የተመለከተውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 9. ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | ፅህፈት ቤት | እስካሁን /ሰኔ 30/ የተቀጠሩ ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ፕረዚደንት ፅ/ቤት | | 3 | 3 |
| 2 | እቅድና ተቋማዊ ማሻሻያ ፅ/ቤት | 1 | 1 | 2 |
| 3 | ሕዝንብና የውጭ ግንኙነት ፅ/ቤት | 2 | 2 | 4 |
| 4 | ውስጥ ኦዲት ፅ/ቤት | 3 | 2 | 5 |
| 5 | ስርኣተ ፆታ ፅ/ቤት | 1 | 1 | 2 |
| 6 | ህግ ፅ/ቤት | 1 | 1 | 2 |
| 7 | ኣካዳሚክና ምርምር ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | | 2 | 2 |
| 8 | ኣስተዳደርና ልማት ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | | 2 | 2 |
| 9 | ሰው ሃብት ልማት ማእከል | 6 | 4 | 10 |
| 10 | ግዥና ንብረት ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 10 | 7 | 17 |
| 11 | የፋይናንስ ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 9 | 6 | 15 |
| 12 | መሰረታዊ ኣገልግሎት ማእከል | 100 | 18 | 118 |
| 13 | የተማሪዎች ዲን | 40 | 187 | 227 |
| 14 | ሬጂስትራር | 3 | 9 | 12 |
| 15 | ቤተመፃህፍት | 24 | 28 | 52 |
| 16 | ኢንፎርሜሽን ማእከል | 3 | 1 | 4 |
| 17 | ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ፅ/ቤት | | 1 | 1 |
| 17 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ | | 5 | 5 |
| 18 | ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ | | 8 | 8 |
| 19 | ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ | | 9 | 9 |
| 20 | ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ | | 6 | 6 |
| 21 | ግብርና ኮሌጅ | | 5 | 5 |
| 22 | ህክምና ኮሌጅ | | 5 | 5 |
| 23 | ክሊኒክ | 9 | 2 | 11 |
| ድምር | | 212 | 315 | 527 |

ዩኒቨርሲቲው እስከ ሰኔ 30 ድረስ 527 ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን ከዚሁም በተጨማሪ 20 ጊዜያዊ (የኮንትራት) ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አሉት። የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 10፤ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | አይነት | እስካሁን /ሰኔ 30/ የተቀጠሩ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ጥበቃ | 5 | | 5 |
| 2 | ግንባታ ፕሮጀክት | 5 | 3 | 8 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ጉልበት ሰራተኛ | 6 | | 6 |
| 4 | ሾፌር | 1 | | 1 |
| ድምር | | 17 | 3 | 20 |

ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ 547 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን አብዛኛዎቹ (ማለትም 58%) ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

## 2.4. የተመደበልን ባጀትና አጠቃቀሙ

ዩኒቨርሲቲው ለ2005 የባጀት (የትምህርት) አመት መደበኛ ባጀት እና ካፒታል ባጀት ተፈቅዶለት በእቅድ የያዛቸውን ተግባራቱን አከናውኗል፡፡

### 2.4.1. መደበኛ ባጀት

የተፈቀደለት የመደበኛ ባጀት በፕሮግራም ባጀት አደላደል መሰረት ለአራት ፕሮግራሞች ማለትም ለአስተዳደር (33978280)፤ ለአካዳሚ (29390000)፤ ለጥናትና ምርምር (4160000)፤ እና ለማህበረሰብ አገልግሎት (1147260) በድምሩ ብር 68675540.00 ተመድቦለታል፡፡ ይህ ባጀት መጀመርያ የተፈቀደለት ባጀት የሚያመላክት ሲሆን አስፈላጊ የባጀት መስተካክሎች ከተደረጉ በኋላ የተፈቀደው ባጀት የሚከተለውን ይመስላል፤ (1) ለፕሮግራም 1 ወይም ለአስተዳደር ነክ ፕሮግራሞች ብር 40004981.73 (2) ለፕሮግራም 2 ወይም አካዳሚ ነክ ፕሮግራሞች ብር 26863723.67 (3) ለምርምር ነክ ፕሮግራሞች ብር 2935000.02 እና (4) ለማህበረሰብ አገልግሎት ነክ ፕሮግራሞች ብር 197150.33 በድምሩ ብር 70000855.75 ተፈቅዱለት ከመደበኛ ባጀት ጋር የተያያዙትን ተግባራት አከናውኗል፡፡ በድምሩ በባጀት አመቱ ከመደበኛ ባጀት በየባጀት አርእስቱ ወጪ የተደረገው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 63519821.31 ነው፡፡ ከዚሁ ውስጥ ቀሪ የሆነው ብር 6481034.44 ሲሆን ለ2006 የግንባታ ብረት መግዣ ይሆን ዘንድ በትምህርት ሚኒስቴር በተላከልን ደብዳቤ መሰረት ወደ አዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ኤጀንሲ ከተላከው አስራ ስድስት ሚልዮን ብር አካል ሆኖ እንዲላክ ስለተደረገ የመደበኛ ባጀት አጠቃቀማችን 100% ሊሆን ችሏል፡፡ ዝርዝር አጠቃቀሙ በሰንጠረዥ 11 ተመልክቷል፡፡ ከሪፖርቱ ማየት እንደሚቻለው የአመቱ የበጀት አጠቃቀም ውጤታማ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በባጀት አመቱ ውስጥ ሁለት የግልፅ ጨረታዎች የተደረጉ ሲሆን ከግልፅ ጨረታ በተጨማሪ ፤ በርካታ ውሱን ጨረታዎች እንዲሁም ብዛት ያላቸው የፕሮፎርማ እና የቀጥታ ግዥዎችን እንዲሁም ከግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማስፈቀድ በርከት ያሉ ማቴርያሎችን የለቀማ ግዥ አከናውነናል፡፡ በግልፅ ጨረታ ብዛት ያላቸው እቃዎች የገዛን ቢሆንም አንዳንድ ያሸነፉ ተወዳዳሪዎች የውጭ ካረንሲ እጥረት በመጥቀስ እና ሎሎች ምክንያቶችን በመግለፅ (ለምሳሌ ማቴርያሉ ከምርት ውጭ ሆነዋል የሚል) ሊያቀርቡልን ባለመቻላቸው አንዳንድ በጣም የምንፈልጋቸው ማቴርያሎችን (ለምሳሌ ስታንድ ባይ ጀነሬተር እና ኮምፒዩተሮች) ማግኘት አልቻልንም፡፡ የመደበኛ ባጀትን (እንዲሁም የካፒታል ባጀት) አጠቃቀም በተመለከተ በተለይ መፃህፍት፤ የላቦራቶሪ ኬሚካሎችን እና ማቴርያሎችን፤ እና የኔትወርክ ማቴርያሎች በለቀማ እንድንገዛ በልዩ ሁኔታ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ ስለፈቀደልን ብዙ ችግሮችን ለማቃለል ችለናል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ኤጀንሲው ላደረገለት እገዛ ምስጋናውን ከወዲሁ ያቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 11. ለ2005 የተፈቀደ እና ጥቅም ላይ የዋለ መደበኛ ባጀት

| የሂሳብ መደብ | መግለጫ | ለ4 ፕሮግራሞች የተፈቀደ (መጀመርያ) | ለ4 ፕሮግራሞች የተፈቀደ (ተስተካክሎ) | ጥቅም ላይ የዋለ | አጠቃቀም በመቶኛ (ከመጀመርያው) | አጠቃቀም በመቶኛ (ከተስተካከለው) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6111 | ለቋሚ ሰራተኞች ደምወዝ | 10680000 | 16479500 | 16476217 | 154.27 | 99.98 |
| 6113 | ለኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | 1104800 | 496401.73 | 540767.83 | 48.95 | 108.94 |
| 6114 | ለቀን ሰራተኞች ምንዳ | 50000 | | 49101.5 | 98.20 | |
| 6115 | ለውጭ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | | | | | |
| 6116 | ለሰራተኞች የሚደረጉ የተለያዩ ክፍያዎች | 1384800 | 247100 | 255630 | 18.46 | 103.45 |
| 6121 | ለቋሚ ሰራተኞች አበል | 934400 | 2069400 | 2068476.81 | 221.37 | 99.96 |
| 6131 | ለቋሚ ሰራተኞች ጡረታ መዋጮ | 854400 | 1398400 | 1328882.39 | 155.53 | 95.03 |
| 6211 | ለደንብ ልብስ ለልብስ ለፍራሽና ኣልጋ ልብስ | 1162800 | 741612.12 | 732930.88 | 63.03 | 98.83 |
| 6212 | ለኣላቂ የቢሮ እቃዎች | 5158300 | 4850904.99 | 4540033.15 | 88.01 | 93.59 |
| 6213 | ለህትመት | 2049400 | 1044517.34 | 771518.97 | 37.65 | 73.86 |
| 6214 | ለኣላቂ የህክምና እቃዎች | 559700 | 192700 | 183290.62 | 32.75 | 95.12 |
| 6215 | ለኣላቂ የትምህርት እቃዎች | 2235000 | 2235000 | 2235000 | 100.00 | 100.00 |
| 6216 | ለምግብ | 12000000 | 13187559.55 | 13175480.96 | 109.80 | 99.91 |
| 6217 | ለነዳጅና ቅባቶች | 1865300 | 1865300 | 1708408.12 | 91.59 | 91.59 |
| 6218 | ለሌሎች ኣላቂ እቃዎች | 1381920 | 1188670 | 744658.12 | 53.89 | 62.65 |
| 6219 | ለተለያዩ መሳርያዎችና መፃህፍት | 1396360 | 1396360 | 1287567.63 | 92.21 | 92.21 |
| 6221 | ለግብርና ለደንና ለባህር ግብኣቶች | 350000 | 350000 | 79220 | 22.63 | 22.63 |
| 6222 | ለእንስሳት ህክምና የሚያገለግሉ | | | | | |
| 6223 | ለምርምርና ለልማት ኣላቂ እቃዎች | 600000 | 600000 | 430371.75 | 71.73 | 71.73 |
| 6231 | ለውሎ ኣበል | 3558820 | 2362793.34 | 2265058.6 | 63.65 | 95.86 |
| 6232 | ለትራንስፖርት ክፍያ | 1926790 | 1539498.34 | 1507774.01 | 78.25 | 97.94 |
| 6233 | ለመስተንግዶ | 2085250 | 1947184 | 1264548.19 | 60.64 | 64.94 |
| 6241 | ለተሽከርካሪዎችና ለሌሎች መጓጓዣዎች እድሳትና ጥገና | 1220000 | 1220000 | 1024199.78 | 83.95 | 83.95 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6243 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ እድሳትና ጥገና | 1148550 | 1148550 | 347205 | 30.23 | 30.23 |
| 6244 | ለህንፃ ለቁሳቁስና ለተገጣጣሚዎች | 241050 | 241050 | 38366.43 | 15.92 | 15.92 |
| 6251 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎቶች | | | | | |
| 6252 | ለኪራይ | 1020000 | 1020000 | 1019879.63 | 99.99 | 99.99 |
| 6253 | ለማስታወቅያ | 332500 | 330416.66 | 235534.63 | 70.84 | 71.28 |
| 6254 | ለመድን ዋስትና | 352000 | 352000 | 351014.9 | 99.72 | 99.72 |
| 6255 | ለጭነት | 320000 | 320000 | 306568.41 | 95.80 | 95.8 |
| 6256 | ለኣገልግሎች ክፍያዎች | 115000 | 115000 | 114007.9 | 99.14 | 99.14 |
| 6257 | ለኤሌክትሪክ ኣገልግሎት ክፍያ | 1320000 | 1720000 | 1691417.02 | 128.14 | 98.34 |
| 6258 | ለቴሌኮሙኒኬሽን ኣገልግሎች ክፍያ | 1563200 | 1563200 | 919114.04 | 58.80 | 58.80 |
| 6259 | ለውሃ ፖስታና ሌሎች ኣገልግሎት ክፍያዎች | 1055000 | 1055000 | 302851.29 | 28.71 | 28.71 |
| 6271 | ለኣገር ውስጥ ስልጠና | 1566500 | 710333.34 | 332353.96 | 21.22 | 46.79 |
| 6272 | ለውጭ አገር ስልጠና | | | | | |
| 6313 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ መግዣ | 3686150 | 3075921 | 2333439.99 | 63.30 | 75.86 |
| 6314 | ለህንፃ ለቁሳቁስ እና ተገጣጣሚዎች መግዣ | 1422650 | 1403483.34 | 1386792.55 | 97.48 | 98.81 |
| 6315 | ለቀንድ ከብቶችና ለመጓጓዣ የሚውሉ | 298900 | 48000 | | | |
| 6412 | ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታና መዋጮ ድጎማ | | | | | |
| 6417 | ለግለሰቦች እርዳታና ስጦታ | 1676000 | 1485000 | 1472139.25 | 87.84 | 99.13 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | 68675540 | 70000855.75 | 63519821.31 | 92.49 | 90.74 |

2.4.2. ካፒታል ባጀት

ከ2005 የባጀት አመት ጀምሮ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ሰራዎችን በራሳቸው እንዲያከናውኑ እና ለዚሁም ተብሎ አስፈላጊው ካፒታል ባጀት እንዲመደብላቸው በተተገበረው አሰራር መሰረት በድምሩ ብር 154284940.00 የካፒታል ባጀት ተመድቦልናል። የተመደበልን ባጀት እና እስከ ሰኔ 30/2005 ያለው ዝርዝር የባጀት አጠቃቀም በሚቀጥለው ገፅ ባለው ሰንጠረዥ (ሰንጠረዥ 12) የተመለከተውን ይመስላል።

ለካፒታል ባጀት መጀመርያ የተፈቀደልን መጠን ከላይ እንደተቀመጠው 154 ሚልዮን ሲሆን አጠቃቀማችን ግን ከዚሁ በላይ ስለነበር ተጨማሪ ባጀት ያስፈልገን ስለነበር በየወቅቱ እንዲስተካከል ተደርጎ (ከአንድ የሂሳብ ባጀት ወደ ሌላ የተደረገውን ዝውውር ጨምሮ) ብር 270833337.55 ያህል ተፈቅዶልናል። የካፒታል ባጀት አጠቃቀምን በተመለከተ እንደነ አርማታ ብረት እና የላቦራቶሪ መሳርያዎችን ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርት ሚኒስቴር በኩል እንዲቀርብልን በተስማማነው መሰረት ከተመደበልን ባጀት ውስጥ ቀንሰን አዛውረን ነበር። ሆኖም ያዛወርነው በሙሉ ጥቅም ላይ ሊውል ስላልቻለ ሃያ ሁለት ሚልዮን ብር ያህል መልሰው ልከውልን ጥቅም ላይ አውለነዋል። በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲያችን በኩል ጥቅም ላይ የዋለው የካፒታል ባጀት መጠን ብር 264863451.1 (ይህም ማለት መጀመርያ ከተፈቀደልን ባጀት 171.67%፤ ተስተካክሎ ከተፈቀደልን ባጀት 97.80% ይሆናል ማለት ነው) ሲሆን ተስተካክሎ ከተፈቀደው ውስጥ ስድስት ሚልዮን ያህል የቀረ ሂሳብ ነበር። ነገር ግን ትምህርት ሚኒስቴር ተዛውሮለት ከነበረለት መጠን ሃያ ሁለት ሚልዮን መልሶ ሲልክልን ለ2006 የባጀት ዘመን ሊሆነን የሚችል አርማታ ብረት በአዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ኤጀንሲ በኩል ተገዝቶ እንዲቀርብልን 16 ሚልዮን ብር (ኤልሲ ለመክፈት) እንድንልክላቸው በተላከልን ደብዳቤ መሰረት ልከንላቸዋል። በዚሁም መሰረት ተስተካክሎ የተላከልን ባጀት በሙሉ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሰንጠረዥ 12. የተፈቀደ ካፒታል ባጀት እና አፈፃፀሙ

| የሂሳብ መደብ | መግለጫ | መጀመርያ የተፈቀደ | ተስተካክሎ የተፈቀደ | ጥቅም ላይ የዋለ | አጠቃቀም በመቶኛ (ከመጀመርያው) | አጠቃቀም በመቶኛ (ከተስተካከለው) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6111 | ለቋሚ ሰራተኞች ደምወዝ | | | | | |
| 6113 | ለኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | 403440 | 435243.00 | 435242.8 | 107.88 | 100.00 |
| 6114 | ለቀን ሰራተኞች ምንዳ | | | | | |
| 6115 | ለውጭ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | 6480000 | 3085239.06 | 3085239.06 | 47.61 | 100.00 |
| 6116 | ለሰራተኞች የሚደረጉ የተለያዩ ክፍያዎች | 22050 | 7352.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6121 | ለቋሚ ሰራተኞች አበል | | | | | |
| 6124 | ለውጭ ኮንትራት ሰራተኞች አበል | 756000 | 126000.00 | 84130.02 | 11.13 | 66.77 |
| 6131 | ለቋሚ ሰራተኞች ጡረታ መዋጮ | 0 | | 0 | | |
| 6211 | ለደንብ ልብስ ለልብስ ለፍራሽና ኣልጋ ልብስ | 59990 | 10000.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6212 | ለኣላቂ የቢሮ እቃዎች | 74710 | 74710.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6213 | ለህትመት | | | | | |
| 6214 | ለኣላቂ የህክምና እቃዎች | | | | | |
| 6215 | ለኣላቂ የትምህርት እቃዎች | | | | | |
| 6216 | ለምግብ | | | | | |
| 6217 | ለነዳጅና ቅባቶች | 96810 | 24000.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6218 | ለሌሎች ኣላቂ እቃዎች | 6280 | 6280.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6219 | ለተለያዩ መሳርያዎችና መፃህፍት | 5270 | 1200.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6221 | ለግብርና ለደንና ለባህር ግብኣቶች | | | | | |
| 6222 | ለእንስሳት ህክምና የሚያገለግሉ | | | | | |
| 6223 | ለምርምርና ለልማት ኣላቂ እቃዎች | 900000 | 150000.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6231 | ለውሎ ኣበል | 11760 | 5900.00 | 5900 | 50.17 | 100.00 |
| 6232 | ለትራንስፖርት ክፍያ | 6125680 | 1020000.00 | 1019903.06 | 16.65 | 99.99 |
| 6233 | ለመስተንግዶ | 572160 | 95200.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6241 | ለተሽከርካሪዎችና ለሌሎች መጓጓዣዎች እድሳትና ጥገና | 80000 | 18000.00 | 695 | 0.87 | 3.86 |
| 6243 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ እድሳትና ጥገና | 30000 | 5000.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6244 | ለህንፃ ለቁሳቁስና ለተገጣጣሚዎች | | | | | |
| 6251 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎቶች | 1560000 | 1560000.00 | 1487675.1 | 95.36 | 95.36 |
| 6252 | ለኪራይ | 72000 | 12000.00 | 1000 | 1.39 | 8.33 |
| 6253 | ለማስታወቅያ | 30000 | 5000.00 | 4200 | 14.00 | 84.00 |
| 6254 | ለመድን ዋስትና | 50000 | 8000.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6255 | ለጭነት | 2704370 | 260000.00 | 260000 | 9.61 | 100.00 |
| 6256 | ለአገልግሎች ክፍያዎች | 80000 | 12000.00 | 4918.09 | 6.15 | 40.98 |
| 6257 | ለኤሌክትሪክ ኣገልግሎት ክፍያ | 0 | | 0 | | |
| 6258 | ለቴሌኮሙኒኬሽን ኣገልግሎች ክፍያ | 14400 | 2400.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6259 | ለውሃ ፖስታና ሌሎች ኣገልግሎት ክፍያዎች | | | | | |
| 6271 | ለኣገር ውስጥ ስልጠና | | | | | |
| 6272 | ለውጭ አገር ስልጠና | | | | | |
| 6313 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ መግዣ | 51512400 | 29150301.00 | 28906716.29 | 56.12 | 99.16 |
| 6314 | ለህንፃ ለቁሳቁስ እና ተገጣጣሚዎች መግዣ | 9200000 | 9200000.00 | 8193470.91 | 89.06 | 89.06 |
| 6315 | ለቀንድ ከብቶችና ለመጓጓዣ የሚውሉ | | | | | |
| 6321 | ለቅድመ ግንባታ ስራዎች | 1181250 | 180000.00 | 0 | 0.00 | 0.00 |
| 6322 | ለመኖርያ ህንጻዎች ግንባታ | 31807000 | 87346700.21 | 86950629.57 | 273.37 | 99.55 |
| 6323 | ለመኖርያ ያልሆኑ ህንጻዎች ግንባታ | 15490010 | 82221910.58 | 78612829.49 | 507.51 | 95.61 |
| 6324 | ለመሰረተ ልማት ግንባታ | 24959360 | 55810901.70 | 55810901.7 | 223.61 | 100.00 |
| 6412 | ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታና መዋጮ ድጎማ | | | | | |
| 6417 | ለግለሰቦች እርዳታና ስጦታ | | | | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | 154284940 | 270833337.55 | 264863451.1 | 171.67 | 97.80 |

## 2.5. የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም

የዩኒቨርሲቲው ግንባታ ሲጠቃለል ከ150 ብሎኮች በላይ ይኖሩታል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን የግንባታ ስራዎች በተለያዩ ፌዞች (ወይም ዙሮች) ነው የሚካሄደው። በዚሁም መሰረት 48 ብሎኮችን የያዘው የመጀመርያው ዙር የህንፃ (አንድ ተቋራጭ እስካሁን ድረስ ስራውን አላጠናቀቀም) እና ተያያዥ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ከአንድ የስራ ተቋራጭ (አንድ የተማሪዎች መዝናኛ ብሎክ፤ አንድ የመማርያ እና ፅ/ቤት ክሎችን የያዘ ብሎክ፤ እና አንድ የሌክቸር ትያትር ብሎክ) በስተቀር ቀሪዎቹ የተጠናቀቀ ሲሆን ሰኔ 2004 አከባቢ የተጀመረው የሁለተኛው ዙር ግንባታ ደግሞ በጥሩ ሁናታ በመከናወን ላይ ይገኛል፤ የተወሰኑቱ አልቀዋል በርከት ያሉት የቀሩት ደግሞ በቅርቡ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል። የሁለተኛው ዙር ግንባታ ስራ የህንፃ ስራዎችና የመሰረተ ልማት ስራዎችን ያጠቃለለ ሲሆን 33 የህንፃ ግንባታ ተቋራጮችና አንድ የመሰረተ ልማት ስራ ተቋራጭ እየተሳተፉበት ይገኛልል። የትራንስፎርመር ቤቶች እና የልብስ ማጠብያ ቦታዎችን ጨምሮ እየተሰሩ ያሉት ብሎኮች 67 ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ብሎኮች ግን 54 ይሆናሉ።

ከስድስት ተቋራጮች በስተቀር (ማለትም ሁለት የራቦራቶሪ ብሎኮች፤ አራት የተማሪ ዶርሚተሩ ብሎኮች፤ አንድ ዎርክሾፕ፤ አንድ የፅ/ቤቶች ብሎክ፤ እና አንድ የሌክቸር ትያትር ብሎክ) ሌሎቹ ብሎኮች በሙሉ እስከ መስከረም 30 ድረስ እንደሚጠናቀቁ ይጠበቃል። ከላይ እንደተጠቀሰው የተወሰኑት ብሎኮች አልቀው የርክክብ ስራ የተጀመረ ሲሆን የ2006 ትምህርት እስኪጀመር ድረስ ክትትሉ የሚቀጥል ሲሆን እስከ መስከረም 30 ድረስ አይጠናቀቁም ተብለው ከተያዙት በሎኮች (ዝርዝሩን በሰንጠረዡ ይመልከቱ) በስተቀር ሌሎቹ በሚቀሩት ወራት ውስጥ የሚጠናቀቁ ይሆናሉ። የሁለተኛው ፌዝ የመሰረተ ልማት ስራዎች ደግሞ በተጓዳኝ በመከናወን ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ የህንፃ ስራዎች በተመለከተ እስከ ሰኔ 30/2005 ያለው አማካይ አፈፃፀም 81.73 ሲሆን በስራ ተቋራጭ ደረጃ ያለው አፈፃፀም ከአንዱ ወደ ሌላው የተለያየ ነው። የአብዛኛዎቹ ብሎኮች አፈፃፀም ከ80% በላይ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ አፈፃፀማቸው ከ60% በታች ነው።

ለ2006 እንቀበላቸዋለን ብለን ያሰብናቸውና ለትምህርትሚኒስቴር ያሳወቅነው የተማሪዎች ብዛት 4400 ነው። እንዲመደቡልን የጠየቅናቸው ተማሪዎች ለማስተናገድ ያስችለን ዘንድ መሟላት ካለባቸው መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ የተማሪዎች መኝታዎች እና የምግብ ቤት አዳራሽ ይገኙበታል። ተጨማሪ የምግብ ቤት አዳራሽ እና ኪችን እየተሰራ ስለሆነ አዲስ ተማሪዎችን እስክንቀበል ድረስ የሚደርስ ይሆናል። የተማሪዎች መኝታ ቤቶችን በተመለከተ ደግሞ በመሰራት ላይ ካሉት ውስጥ 14 (እያንዳንዳቸው 204 ተማሪዎችን መያዝ የሚችሉ) እና 2 (እያንዳንዳቸው 400 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችሉ) እስከ መስከረም 30 የሚጠናቀቁ ይሆናሉ። ከዚሁም በተጨማሪ ቀደም ብለው ከተጠናቀቁት ውስጥ ክፍት መኖርያ ቤቶች ስላሉን ለ2006 የትምህርት ዘመን ለምንቀበላቸው ተማሪዎች በቂ ይሆናሉ። ዝርዝር የግንባታ አፈፃፀሙም በሰንጠረዥ 13 እና 14 በሚቀጥሉት ገፆች ተጠቃልለው ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 13. የህንፃ ስራዎች አፈፃፀም (እስከ ሰኔ 30/2005)

| No | Name of Contractor | Typology | Contract Amount | Vat | Vat | Contract Amount with Vat | Executed % | Executed Amount | May not be completed by Meskerem 30/2006 E.C. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Abrahaley Belay G.C | LAB-T1-141 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **94.86** | 5,966,515.30 | |
| | | LN-T1-366 | 456,417.93 | 68,462.69 | 68,462.69 | 524,880.62 | **100.00** | 456,417.93 | |
| 2 | Aklilu Asefa B.C | SE-M1-153 | 6,649,474.20 | 997,421.13 | 997,421.13 | 7,646,895.33 | **86.02** | 5,719,978.78 | |
| 3 | Amanuel Gedlu B.C | LAB-T1-145 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **66.21** | 4,164,706.71 | X (Laboratory) |
| | | LAB-T1-146 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **66.46** | 4,180,512.04 | X (Laboratory) |
| 4 | Araya Wube G.C | Do-T1/Tv-202 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **97.48** | 6,187,580.11 | |
| 5 | Ataklti Belay Fantu B.C | Do-T1/Tv-216 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **100.00** | 6,347,818.08 | |
| 6 | Belay Negash G.C | CL-D1-154 | 5,159,608.75 | 773,941.31 | 773,941.31 | 5,933,550.06 | **68.43** | 3,530,819.33 | |
| | | WS-T1-162 | 2,349,621.83 | 352,443.27 | 352,443.27 | 2,702,065.10 | **50.38** | 1,183,778.01 | X (Workshop) |
| 7 | Brhane G/Mariam GC & WC | LAB-T1-167 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **98.96** | 6,224,669.16 | |
| | | WS-T1-164 | 2,349,621.83 | 352,443.27 | 352,443.27 | 2,702,065.10 | **100.00** | 2,349,621.83 | |
| 8 | Brothers Engineering B.C | LI-T1-100 | 10,764,398.07 | 1,614,659.71 | 1,614,659.71 | 12,379,057.78 | **86.74** | 9,337,464.08 | |
| 9 | Daniel kiros B.C | LAB-T1-140 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **84.48** | 5,313,886.53 | |
| | | LN-T1-367 | 456,417.93 | 68,462.69 | 68,462.69 | 524,880.62 | **100.00** | 456,417.93 | |
| 10 | Fantaye Gidey B.C | Do-T1/Tv-235 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **66.98** | 4,251,552.09 | X (Dormitory) |
| 11 | Getachew Tadesse & Zelalem Tadesse B.C | SE-M1-150 | 6,649,474.20 | 997,421.13 | 997,421.13 | 7,646,895.33 | **87.51** | 5,818,839.17 | |
| | | TL-T1-106 | 1,296,449.26 | 194,467.39 | 194,467.39 | 1,490,916.65 | **95.14** | 1,233,453.36 | |
| 12 | Gizen G.C | Do-T1/Tv-228 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **81.65** | 5,182,679.88 | |
| | | Do-T1/Tv-229 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **75.74** | 4,807,836.14 | |
| 13 | Goitom W/gebriel Construction | AM-T1-XX-19 | 8,633,676.37 | 1,295,051.46 | 1,295,051.46 | 9,928,727.83 | **61.73** | 5,329,665.12 | |
| | | DN-T1-18 | 4,210,868.01 | 631,630.20 | 631,630.20 | 4,842,498.21 | **83.55** | 3,518,205.49 | |
| | | KI-T1-17 | 6,277,603.96 | 941,640.59 | 941,640.59 | 7,219,244.55 | **70.78** | 4,443,112.31 | |
| 14 | H/Mariam Hiluf B.C | Do-T1/Tv-233 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **95.18** | 6,042,029.08 | |
| | | Do-T1/Tv-234 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **89.74** | 5,696,428.48 | |
| 15 | H/Miceal Desta G.C | LAB-T1-166 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **75.38** | 4,741,601.56 | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | LN-T1-358 | 456,417.93 | 68,462.69 | 68,462.69 | 524,880.62 | **99.20** | 452,781.42 | |
| 16 | Haftom W/Gebriel B.C | LAB-T1-171 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **74.44** | 4,682,331.54 | |
| | | LN-T1-359 | 456,417.93 | 68,462.69 | 68,462.69 | 524,880.62 | **99.20** | 452,781.42 | |
| 17 | Kahsay Atsbaha B.C | CL-D1-149 | 5,159,608.75 | 773,941.31 | 773,941.31 | 5,933,550.06 | **67.92** | 3,504,348.99 | |
| | | LAB-T1-142 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **65.49** | 4,119,266.36 | |
| 18 | kalka Construction B.C | Do-T1/Tv-200 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **79.18** | 5,026,494.99 | |
| | | Do-T1/Tv-263 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **68.83** | 4,369,189.22 | |
| 19 | Kassahun Mehari B.C | SE-M1-151 | 6,649,474.20 | 997,421.13 | 997,421.13 | 7,646,895.33 | **85.25** | 5,668,459.98 | |
| 20 | Kibralem Mebrahtu B.C | DHB-T2-101 | 4,007,708.80 | 601,156.32 | 601,156.32 | 4,608,865.12 | **74.68** | 2,993,057.53 | X (Office) |
| | | LH-D1-105 | 2,313,167.99 | 346,975.20 | 346,975.20 | 2,660,143.19 | **68.82** | 1,591,906.25 | X (LTH) |
| 21 | Kibrom Desta B.C | Do-T1-CYT-201 | 9,855,207.54 | 1,478,281.13 | 1,478,281.13 | 11,333,488.67 | **86.30** | 8,505,459.01 | |
| 22 | Mekonnen W/Rufeal B.C | DAB-T2-102 | 4,125,821.19 | 618,873.18 | 618,873.18 | 4,744,694.37 | **92.30** | 3,808,278.19 | |
| | | LH-D1-103 | 2,313,167.99 | 346,975.20 | 346,975.20 | 2,660,143.19 | **96.68** | 2,236,370.35 | |
| 23 | Mulugeta Tadesse B.C | Do-T1/Tv-222 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **82.59** | 5,242,495.37 | |
| | | Do-T1/Tv-223 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **71.36** | 4,530,026.43 | |
| 24 | Nebyu kiros B.C | SE-M1-152 | 6,649,474.20 | 997,421.13 | 997,421.13 | 7,646,895.33 | **88.63** | 5,893,332.57 | |
| | | LH-D1-104 | 2,313,167.99 | 346,975.20 | 346,975.20 | 2,660,143.19 | **86.24** | 1,994,908.23 | |
| 25 | Niat B.C | Do-T1-CYT-230 | 9,855,207.54 | 1,478,281.13 | 1,478,281.13 | 11,333,488.67 | **46.25** | 4,557,638.29 | X (Dormitory) |
| | | Do-T1/Tv-232 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **59.72** | 3,790,972.82 | X (Dormitory) |
| 26 | Nigus Aynimishet B.C | Do-T1/Tv-227 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **100.00** | 6,347,818.08 | |
| 27 | Solomon Abraha BC | LAB-T1-143 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **76.39** | 4,804,822.92 | |
| | | LAB-T1-144 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **75.55** | 4,752,138.45 | |
| 28 | Tadelle Berhe B.C | Do-T1/Tv-226 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **89.84** | 5,703,074.64 | |
| | | WS-T1-164 | 2,349,621.83 | 352,443.27 | 352,443.27 | 2,702,065.10 | **95.12** | 2,234,959.11 | |
| 29 | Teklebrhan Tadesse B.C | Do-T1/Tv-262 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **62.68** | 3,979,059.30 | X (Dormitory) |
| 30 | Teklu W/Miceal B.C | Do-T1-CYT-231 | 9,855,207.54 | 1,478,281.13 | 1,478,281.13 | 11,333,488.67 | **79.53** | 7,837,858.38 | |
| | | Do-T1/Tv-225 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | **82.92** | 5,263,763.10 | |
| 31 | Tsigabu G/Slassie G.C | LAB-T1-172 | 6,289,930.97 | 943,489.65 | 943,489.65 | 7,233,420.62 | **78.36** | 4,928,631.40 | |
| | | LN-T1-360 | 456,417.93 | 68,462.69 | 68,462.69 | 524,880.62 | **58.37** | 266,412.29 | |
| 32 | Welday Haylu B.C | Do-T1-CYT-203 | 9,855,207.54 | 1,478,281.13 | 1,478,281.13 | 11,333,488.67 | **99.64** | 9,820,023.46 | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 33 | Yared Mehari G.C | CC-T1-XX-12 | 4,381,811.09 | 657,271.66 | 657,271.66 | 5,039,082.75 | **81.79** | 3,583,955.15 | |
| | | BA-T2-24 | 1,530,372.32 | 229,555.85 | 229,555.85 | 1,759,928.17 | **93.89** | 1,436,942.48 | |
| | | BA-T1-23 | 1,142,010.95 | 171,301.64 | 171,301.64 | 1,313,312.59 | **89.48** | 1,021,832.80 | |
| አማካይ | | | 309,733,453.54 | 46,460,018.03 | 46,460,018.03 | 356,193,471.57 | **81.73** | 247886979.03 | |

### ሰንጠረዥ 14. የመሰረተ ልማት ስራዎች አፈፃፀም

| No | Name of Contractor | Typology | Contract Amount | | | **Executed %** | Executed Amount |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | United Construction P.L.C | Lot-1A | 52,225,068.34 | | | **100.00** | 52,225,068.34 |
| | | Lot-1B | 29,979,674.24 | | | **100.00** | 29,979,674.24 |
| | | Transformer houses | 8,196,404.77 | | | **90.00** | 7,376,764.29 |

## 3 የእቅድ አፈፃፀም

ዩኒቨርሲቲው በ2004 የባጀት አመት ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከደረሱበት ደረጃ ተነስተን ወደፊት እንጓዝ የሚል መሪ ቃል ይዞ ተግባራቱን ያከናወነ ሲሆን በ2005 የባጀት አመት ደግሞ የ2004 አፈፃፀኘ በመገምገም የአመቱ ቁልፍ ተግባር በማስቀመጥ እና ዝርዝር እቅድ በማውጣት እና መግባባት በመፍጠር ነው ስራውን የጀመረው። የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የ2005 ቁልፍ ተግባር ***"አዲስ ተማሪዎችን ለሁለተኛ ጊዜ በአግባቡ መቀበልና ማስተናገድ፤ እንዲሁም የተቛማዊ ለውጥ እና የመልካም አስተዳደር ንቅናቄዎችን መሰረት በማድረግ የትምህርተ ሰራዊት ግንባታ ስራዎችን ማከናወን"*** የሚል ነው።

የ2005 የትምህርት/የባጀት ዘመን ስራዎች የተከናወኑት ***"መጠናከርና መስፋፋት"*** ወይም Consolidation and Expansion በሚል መሪ ቃል ስር እቅድ በማውጣትና እና በእቅዱ ዙርያ ሰፊ ውይይት ተደርጎበት እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ ሲሆን ከሐምሌ 1/2004 እስክ ሰኔ 30/2005 ባሉት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ በዩኒቨርሲቲው የተከናወኑት ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ከእቅዱ ጋር በማነፃፀር በሰንጠረዥ መልክ ቀርቧል። ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታው ነጥብ በነጥብ በሰንጠረዥ መልክ የቀረበ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ሶስት ተልእኮዎች (ማስተማር፤ ምርምር፤ እና የህብረተሰብ አገልግሎት) በተመለከተ የተሰሩት ዋና ዋና ስራዎች አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

### 3.1. መማር ማስተማር

የማስተማር ስራዎችን በተመለከተ በ2005 ከሶስት ሺ በላይ አዲስ ተማሪዎችን በመቀበል የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ብዛት በአንድ አመት ውስጥ በአራት እጥፍ ያደገ ሲሆን ሁለት አዳዲስ ኮሌጆችም ተመስርተው ተማሪዎችን ተቀብለው በማስተማር ላይ ይገኛሉ። በተለይ የህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለማቋቋም የጠየቀው ጥረት ከፍተኛ ነበር። በከተማው ከሚገኝ ሆስፒታል፤ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ስር ካለው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ፤ እና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ተባብሮ መስራትን የሚጠይቅ ስራ ነው የነበረው። በዚሁም መሰረት ከዓዲግራት ሆስፒታል ጋር በቅንጅት ለመስራት መግባባት ላይ የተደረሰበት ሲሆን የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ደግሞ የማቴርያል ድጋፍን ጨምሮ ቆንጆ እገዛ አድርጎልናል። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ደግሞ ሶስት (አንዱ አቋርጦ የሄደ ቢሆንም) ሜዲካል ዶክተሮችን መድቦልናል።

በአመቱ ቁልፍ ተግባር የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ መሆኑ በተያዘው መሰረትም የተማሪዎች፤ የመምህራንና የሰራተኞች የአንድ ለአምስት ቡድኖች እንዲቋቋሙ በተሟላ መልኩ ባይሆንም በተለይ የተማሪዎች አንድ ለአምስት መረቦች የተኛለ እንቅስቃሴ አሳይተዋል። የተማሪዎች መረቦችን ስራ ለማጠናከር ያህል በዩኒቨርሲቲው ላይብረሪ ከሚገኙ አዳራኛች ውስጥ አንዱ ለዚሁ ተብሎ ተመድቦ ተማሪዎች ሲጠቀሙበት ከርመዋል። የድጋፍና ክትትል ስራዎችም ተሰርተዋል። ሆኖም ስራው በተፈለገው ደረጃ የደረሰ ስላልሆነ በ2006 የትምህርት ዘመንም የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል። በዩኒቨርሲቲው የተቋቋሙ የአንድ ለአምስት ቡድኖች በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፤

ሰንጠረዥ 15፤ የተማሪዎች፤ የመምህራንና የሰራተኞች አንድ ለአምስት ቡድኖች

| ኮሌጅ / ፅህፈት ቤት | የተማሪዎች 1 ለ 5 ቡድኖች | | | የመምህራን 1 ለ 5 | የድጋፍ ሰጪ 1 ለ 5 | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1ኛ አመት | 2ኛ አመት | ድምር | | | |
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ | 245 | 60 | 305 | 11 | 1 | 317 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ | 82 | 40 | 122 | 18 | 1 | 141 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 30 | | 30 | 3 | 1 | 34 |
| ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ | 23 | | 23 | 3 | 1 | 27 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ | 77 | 25 | 102 | 4 | 1 | 107 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | 49 | 14 | 63 | 13 | 1 | 77 |
| ደጋፍ ሰጪ ፅ/ቤቶች | | | | | 88 | 88 |
| ድምር | 506 | 139 | 645 | 52 | 94 | 791 |

3.2. የምርምር እና ህብረተሰብ አገልግሎት ስራዎች

የምርምር ስራዎችን በተመለከተ በተመለከተ በ2004 የተደረጉ ጥናቶች በ2005 የምርምሮች ማቅረብያ ቀን (Research Rreview Day) በመሰየም የተጠናቀቁ ምርምሮች ቀርበው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል። የ2005 የምርምር ፕሮፖዛሎችን በተመለከተ ደግሞ በ2004 የፕሮፖዛሎች መረጣ የተካሄደው በዩኒቨረሲቲ ደረጃ ሲሆን ዘንድሮ መረጣው በዋናነት በኮሌጅ ደረጃ እንዲካሄድ ተደርጓል። ለባጀት አመቱ 71 የምርምር ፕሮፖዛሎች ቀርበው በየኮሌጁ መረጣ ተደርጎ ከተጣሩ በኋላ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ 23 የምርምር ፕሮፖዛሎች ተቀባይነት አግኝተው በመሰራት ላይ ይገኛሉ። ለምርምር ስራዎቹ የተመደበው ገንዘብ ደግሞ 1.6 ሚልዮን በመሰራት ላይ የሚገኙት ምርምሮች በሚከተለው ሰንጠረዥ የቀረቡት ናቸው። ከዚሁም በተጨማሪ ከትግራይ ክልል የፋይናንስና ፕላን ቢሮ እና የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በመተባበር በተቀናጀው የፓኬጅ ፕሮግራም አተገባበርና ውጤት የሚያተኩር ምርምር በዩኒቨርሲቲው እየተደረገ ይገኛል። የምርምሩ ባጀት አንድ ሚልዮን ሲሆን ባጀቱም የተገኘው ከክልሉ የፋይናንስና ፕላን ቢሮ ነው።

የማህበረሰብ አገልግሎት ሌላው የዩኒቨርሲቲው ተልእኮ ሲሆን ይሄንን በተመለከተም ዩኒቨርሲቲው በርካታ ስራዎችን አከናውኗል። በዋናነት እነዚህን መጥቀስ ይቻላል፤

(1) በክልል ደረጃ በከተማው የሚከበረው የመስቀል በአል በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር የሩጫ ውድድር እና የፓነል ውይይት አዘጋጅቷል፡

(2) የከተማው ስፖርት ክበብ ለማጠናከር የገንዘብ ድጋፍ ተሰጥቷል፡

(3) ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ቅርበት ያላቸው የዓፋር ክልል ወረዳዎች ማለትም ዳሉል፡ በራሕለ፡ ኮነባ፡ እና አብዓላ በትምህርት ዘርፍ ድጋፍ ለመስጠት ከወረዳ አስተዳዳሪዎች እና ከትምህርት ፅ/ቤት ሃላፊዎች ሁለት የውይይት መድረክ የተካሄደ ሲሆን ተግባራዊ ስራዎችን ለመስራት ዝግጅቶች በመደረግ ላይ ናቸው፡

(4) የዓዲግራት ሆስፒታልን በህክምና መሳርያዎች ለማጠናከር ስዊድን ከሚገኘው ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመስማማት እና የትራንስፖርት ወጪውን በመሸፈን አራት ኮንተይነሮች ሙሉ የህክምና እቃዎች አስመጠተን ድጋፍ አድርገናል ፤ ሆስፒታሉ በነዚህ ማቴርዩሎች አመካኝነት በርካታ ችግሮችን ሊያቃልል እንደሚችል የሚታመንበት ሲሆን ከዩኒቨርሲቲው ጋር ያለው ግንኙነትም የጠበቀ እና የመደጋገፍ መንፈስ የሰፈነበት እንደሚሆን ያደርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከጣልያን አገር (ኤስ ኦ ከሚባል ድርጅት) ከተበረከተልን ያገለገለ አምቡላንስ ጋር የመጡ የህክምና መሳርያዎች (የኦፕሬሽን ቴብል እና ስተሪላይዘሮች) ለሆስፒታሉ አበርክተናል፤

(5) በምስራቃዊ ዞን ለሚገኙ 208 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህራኖቻቸው የተዘጋጀ 500 የፈተና ጥራዝ አባዝተን አሰራጭተናል።

(6) ከ300 በላይ ለሚሆኑ ከትግራት ምስራቃዊ ዞን እና ከዓፋር አጎራባች ወረዳዎች ለተውጣጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እና የትምህርት አመራር ባለሞያዎች በሳይንስና ሂሳብ ትምህርቶች ጥራት ዙርያ የሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናው የክልሉ የትመህርት ቢሮ ሃላፊን ጨምሮ በተጋበዙት ባለሞያዎችና በዩኒቨርሲቲው መምህራን የተሰጠ እና ውጤታማ ነበር።

ሰንጠረዥ 16፤ ፀድቀው በመሰራት ላይ ያሉ የምርምር ርእሶችና የተመደበላቸው በጀት

| S.No. | Research Title | Principal Investigator | College | Department of PI | Budget Allocated |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Characterization and Determinations of Dairy Production in Eastern Zone | Gebrekidan Tesfay | CAES | Animal Prodn and Tech | 46116.1 |
| 2 | Making of Bakery Products using Composite Food: Wheat and Beles Cladodes | Amlisha Mezgebe | CAES | Plant Science | 65146.2 |
| 3 | Traditional Gold Mining as a Challenge for Watershed Management: Case of Werie Basin | Hagos Gebreselassie | CAES | Natural Resource Management | 98708.4 |
| 4 | Assessment on Major Health Constraints and Production System of Market Oriented Livestock Development: GantaAfeshum | Dr. Berihu Haftu | CAES | Animal Prodn and Tech | 57737 |
| 5 | Incidence of Poverty and Tourism Development in Tigray: Eastern Zone | Araya Mebrahtu | CBE | Economics | 58475 |
| 6 | Effect of Drought Risk Management and Coping Strategy on Welbeing of Rural Households in Tigray | Simon Tareke | CBE | Accounting and Finance | 51399.3 |
| 7 | Impact of Controlled Grazing Technique on Livelihood of Rural Communities | Abiy Kassa | CBE | Economics | 59061.55 |
| 8 | Assessing the Performance of Urban Land Lease Policy Implementation and Practices in Tigray | Yibrah Hagos | CBE | Economics | 69936.67 |
| 9 | Application and Enhancement of Quality Engineering on Manufacturing Industries of Tigray | Esubalew Aweke | CET | Electrical Engineering | 134860.75 |
| 10 | A Feasibility Study of Solar PV and Wind Power Generation for Rural Electrification of Tigray | Gebretsadkan Teklay | CET | Electrical Engineering | 191288.68 |
| 11 | Assessment on the Construction Problems of the ten new Universities: case of four universities | Dessie Ayelgn | CET | Civil Engineering | 58040 |
| 12 | Sustainable Solid Waster Management System: Adigrat | Kiros Teklehaimanot | CET | Chemichal Engineering | 42145 |
| 13 | Comparison of Mineral Contents and Physiochemical Properties of White and Red Honies: Degua Tembien | Tassew Alemayehu | CNCS | Chemistry | 69596.8 |
| 14 | Determinants of Quality Adulteration Effects of Honey from Adigrat and Surrounding Areas | Tadesse Gebremariam | CNCS | Chemistry | 43856.5 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 15 | Indigenous Soil Classification by Farmers: Case of Gulomekada and Kilteawlaelo | Tesfay Teka | CNCS | Chemistry | 68060 |
| 16 | Nutrition and Medicinal Values of Cactus around Adigrat | Kassa Belay | CNCS | Chemistry | 88145 |
| 17 | Evaluation of Surface Water Quality and its Suitability for Irrigation | Girma Kassa | CNCS | Geology | 66629.5 |
| 18 | Bacteriological and Physiological Quality of Drinking Water and Hygine/Sanitation in Adigrat | Mesfin Ayenew | CNCS | Biology | 61000 |
| 19 | Challenges and Success in Implementation of Government Budget System: Case of Tigray | Alem Zeray | CSSH | Geography and Env. Studies | 61000 |
| 20 | Students of SSH Reluctance to Join the Department of English: Adigrat and Axum | Gebrewahid Tsige | CSSH | Eglish | 41671 |
| 21 | Contribution of Scientific Research Collaboration and Publications for R&D in Tigray | Teklebirhan Berhe | CSSH | Psychology | 59708.6 |
| 22 | Assessing Dimensionality and Validity of Teachers Performance Evaluation in Eastern Zone High Schools | Samuel Embiza | CSSH | Psychology | 39986 |
| 23 | Assessment on the Implementation of Students' Score Based Evaluation Systerm and its Impact in Tigray Schools | Amanuel Weldemichael | CSSH | English | 80100 |
| **Total** | | | | | **1612668.05** |

የ2005 የባጀት አመት አጠቃላይ የስራ የኣፈፃፀም ሰንጠረዥ

| ግቦች | ሊሰሩ የታቀዱ ዝርዝር ስራዎች | የዘጠኝ ወራት አፈፃፀም ማብራርያ | እቅዱን በመፈፀም ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ሁናታዎች | የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. ኣዲስ ተማሪዎችን ለሁለተኛ ጊዜ ለመቀበል ኣስፈላጊ ዝግጅቶችን በማድረግ ትምህርት መጀመርና ማካሄድ | የግንባታ ስራዎች፤ የመሰረተ ልማት ስራዎች እና ለህንፃው ኣስፈላጊ የሆኑት ፈርኒቸሮችና ሌሎች ማቴርያሎች ኣቅርቦት በተመለከተ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ | አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ከ2005 የባጀት አመት ጀምሮ የግንባታ ስራዎችን በራሳቸው እንዲከታተሉና ባጀታቸውን እንዲያስተዳድሩ በተደረሰው ስምምነት መሰረት ዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት አደራጅቶ የክትትል ስራዎችን ሰርቷል። ከኮንትራክተሮች ጋር በተደጋጋሚ በመገናኘት ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን የግንባታ አፈፃፀምና ክትትል ስራዎች በተሻለ ቅልጥፍና እየተሰራ ይገኛል። ከዚሁም በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው ከ3200 አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል በያዘው እቅድ መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ማቴርያሎች /አልጋ፤ ፍራሽ፤ ወንበር/ በግዥ መልክ እንዲቀርቡ ተደርጓል። | መጀመርያ እንዲገዙ የተደረጉ ወንበሮች በቂ ሆነው አልተገኙም። በተለይ የላይብረሪ እና የዶርሚተሪ ወንበሮች እጥረት አጋጥሟል። የካፒታል ባጀት እጥረት አጋጥሟል። | ተጨማሪ ግዥዎች ተደርገው የወንበር እና የጠረጴዛ እጥረት እንዲቃለል ተደርጓል። ተጨማሪ የካፒታል ባጀት ጠይቀን ስለተፈቀደልን የካፒታል ባጀት እጥረቱ ተፈቷል። |
| | የሰው ሃይል ልማት ማጠናከር | ቀደም ብሎ ፀድቆ ሲሰራበት የነበረው መዋቅር በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ አዲስ መዋቅር እንዲፀድቅ ተደርጎ በዚሁም መሰረት የሰራተኛ ድልድል የተጠናቀቀ ሲሆን የአዲስ ሰራተኞች ቅጥርም በአዲሱ መዋቅር መሰረት በመደረግ ተከናውኗል። የቅጥር ስራ እንደአስፈላጊነቱ እየታየ በ2006ም የሚቀጥል ይሆናል። መዋቅሩ በፀደቀበት ወቅት ሳይፀድቁ የቀሩ (ለምሳሌ የጉልበት ሰራተኞች) ስለነበሩ ተፈላጊ ሰራተኞች መቅጠር አልተቻለም ነበር። ሆኖም ጥያቄው ተልኮ እንዲፀድቁ ተደርገዋል። ስልጠናን በተመለከተ የተለያዩ ስልጠናዎችም ለመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተሰጥተዋል። ከስልጠናዎች በተጨማሪም የልምድ ልውውጦች ተከናውነዋል። በዚሁም መሰረት ለ21 ሰራተኞች ከዩኒቨርሲቲው ውጭ የተለያዩ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን 98 ሰራተኞች ደግሞ በተለያዩ ቦታዎች (አብዛኛዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች) የልምድ ልውውጥ አግኝተው ተመልሰዋል። | ተፈላጊ ሆነው ያልፀደቁ ስራ መደቦች አጋጥመዋል | ተጨማሪ የስራ መደቦች እንዲፈቀድልን ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ጥያቄ አቅርበን ፀድቆ ተልኮልናል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የአመቱን የትምህርት መርሃግብር ማውጣትና ማፅደቅ | የአመቱ መርሃ ግብር በጊዜው ወጥቶ ተተግብሯል | | |
| | ለአዲስ ተማሪዎች ኦርየንቴሽን መስጠት፤ የትምህርት ክፍል ምደባና፤ የትምህርት ፕሮግራሞች ማሳወቅ | በእቅዱ መሰረት ለአዲስ ተማሪዎች አስፈላጊው ኦርየንቴሽን በመስጠት የትምህርት ክፍል ምደባ ተደርጓል። በትምህርተ ክፍል ምደባ ወቅት 25% የሚሆኑ ቦታዎች ለሴቶች ያለውድድር እንዲደለደሉ ተደርጓል። | | |
| | የአመራር አቅም መገንባት | በየደረጃው ለሚገኙ የዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት የተለያዩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። የዩኒቨርሲቲውን ስትራቴጂክ ፕላን ለማዘጋጀት ይረዳ ዘንድ በየደረጃው ላሉት ሃላፊዎች ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ በመጡ ባለሞያ የቢኤስሲ ስልጠና ተሰጥቷል። የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን በተመለከተ ደግሞ በየደረጃው ለሚገኙ ሃላፊዎች ከትምህርት ሚኒስቴር በመጡ ባለሞያ ስልጠና ተሰጥቷል። የኦዲት ስራዎችን በተመለከተ ደግሞ ለውስጥ ኦዲት ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል። ከዚሁም በተጨማሪ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ለልምድ ልውውጥ ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ሄደው ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል። | | |
| | መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ከአገር ውስጥም ከውጭ አገርም መቅጠር፤ የፅዳት ስራን ወደውጭ መስጠት | በተያዘው የመስፋፋት እቅድ መሰረት በርካታ መምህራን በቅጥርና በዝውውር እንዲሚሉ ተደርጓል። ከዚሁም በተጨማሪ 11 የህንድ መምህራን ተቀጥረው በስራ ላይ ይገኛሉ። በሁለተኛ ሰሚስተር ደግሞ መቐለ ዩኒቨርሲቲ ይሰራ የነበረ ህንድ መምህር ወደና መጥቶ በመስራት ላይ የሚገኝ ስለሆን በድምሩ 12 የህንድ መምህራን ከኛ ጋር በመስራት ላይ ይገኛሉ። የፅዳት ስራ ወደ ውጭ የማውጣቱ ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ በጨረታ መልክ ወጥቶ ከሁለተኛ ሰሚስተር ጀምሮ በከተማው ለሚገኝ በጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጀ ማህበር አስፈላጊው ውል ተገብቶ እንዲሰጥ የተደረገ ሲሆን እስካሁን በጥሩ ሁኔታ እየተሰራ ይገኛል። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የተጠናከረ የማባዣ ክፍል በማደራጀት ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙትን መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች ማዘጋጀትና ማቅረብ፡ መፃህፍትን በሶፍት ኮፒ ማሰባሰብ | የማባዣ ክፍሉ በጥሩ ሁኔታ መፃህፍቶችን በማባዛት እያቀረበ ይገኛል። ከዚሁም በተጨማሪ መፃህፍትን በለቀማ እንድንገዛ ከግዥና ንብረት አስተዳደር በተሰጠን ፈቃድ መሰረት በአመቱ ሁለት ጊዜ በለቀማ በርካታ መፃህፍት ተገዝተዋል። በእገዛ መልክም መፃህፍት የተገኙ ሲሆን (አሜሪካን አገር ከሚገኙ የአከባቢው ተወላጅ 50 መፃህፍት ተልከውልናል) በሶፍት ኮፒ ከመምህራን የሚገኙ መፃህፍትም እየተባዙ እንዲቀርቡ እየተደረጉ ነው። | የመፃህፍት አጥረት አሁንም ያልተቀረፈ ችግር ነው | የካቲት ወር ላይ በወጣው ሁለተኛው ግልፅ ጨረታ ተወዳዳሪዎች ቀርበው አሸናፊው የተለየ ቢሆንም ሊያቀርብልን ስላልቻለ ሰኔ ላይ በለቀማ እንዲገዙ ተደርገዋል። |
| | የተከላ ሳምንት በመወሰን የዩኒቨሲቲው ህብረተሰብ በስፋት የሚሳተፍበትና በባለሞያዎች የተደገፈ ተክሎችን የመትከል ስራ ማከናወን | የተከላ ስራ ክረምት 2004 ላይ ተከናውኗል። በተከላው ወቅት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች እና ሰራተኞች በስፋት ተሳትፈውበታል። በድምሩ 20000 ያህል የተለያዩ ተክሎች ተተክለዋል። ሁሉም ፀድቀዋል። | | |
| | የዩኒቨርሲቲው አንደኛ አመት ምስረታ በደማቅ ሁናቴ ማክበር | የተከበሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን እና የተከበሩ የክልሉ ፕረዚደንት አቶ አባይ ወልዱ በተገኙበት ህዳር 22/2005 ዩኒቨርሲቲው በይፋ የተመረቀ ሲሆን ከምረቃው ጋር ተያይዞ የምስረታው አንደኛ አመት በደማቅ ሁናታ ተከብሯል። ከምረቃው እና የአንደኛ አመት አከባበሩ ጋር ተያይዞ ዩኒቨርሲቲው ያዘጋጀው እና በርካታ ባለሞያዎች የተገኙበት የመጀመርያ ሃገራዊ ኮንፈረንስ በበለስ ላይ ተካሂዷል። | | |
| | ለመምህራን መኖርያ የሚሆኑ ኮንደሚንየም ቤቶች የሚገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት | ለመምህራን መኖርያ የሚሆኑ ኮንደሚንየም ቤቶች ለመግዛት በከተማው ያሉት ኮንደሚንየሞች ያላላቁ /ግንባታቸው ያለቀው ቀደም ብለው የተከፋፈሉ በመሆኑ/ በመሆናቸው እና ግንባታቸው በመቋረጡ 11 ያላለቁ ኮንደሚንየሞችን ባሉበት ሁኔታ ለመግዛት ከክልሉ ቤቶች ኤጀንሲ ጋር በተደረሰው መግባባት መሰረት ለግዥው የሚሆን ገንዘብ (ማለት 18 ሚልዮን) እንዲፈቀደልን ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄ አቅርበን እስካሁን አልተፈቀደልንም። | ለመምህራን መኖርያ የሚሆኑ ያላለቁ ኮንደሚንየሞች መግዣ ተጨማሪ ገንዘብ ተጠይቆ ያልተፈቀደ መሆን | ለ2006 ባጀት እንዲያዝ አድርገናል። በዚሁም መሰረት በ2006 የሚከፈል ይሆናል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 2. ተቋማዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈንና ማስጠበቅ | የዩኒቨርሲቲው አመታዊ እቅድ ማዘጋጀትና በአመታዊ ዝርዝር እቅዱ መወያየትና መግባባት መፍጠር | ዩኒቨርሲቲው አመታዊ እቅዱን ሃምሌ 2004 ላይ አዘጋጅቶ በቦርድ ውይይት ተደርጎበት እንዲጻብር ከተደረገበት በኋላ ከመስከረም 11 – 13 በተደረገው አጠቃላይ የመምህራንና ሰራተኞች ስብሰባ ቀርቦ ተጨማሪ ውይይት ተደርጎበት መግባባት ላይ ተደርሶበታል። መምህራንና ሰራተኞችን በሙሉ ያሳተፈ የስድስት ወራት የአፈፃፀም ግምገማ የካቲት 22/2005 ተደርጎ ውይይት ተደርጎበታል። በቀሩት ወራት ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ አፅንኦት ተሰጥቶባቸዋል። በአመቱ መጨረሻም በየደረጃው ግምገማ የተደረገ ሲሆን ሁሉም መምህራንና ሰራተኞች በተገኙበት ሰኔ 29/2005 የአንድ ቀን ግምገማ ተደርጎ የአመቱ ስራዎች ተገምግመዋል። | | |
| | የዩኒቨርሲውን እቅድ መሰረት በማድረገ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የየራሳቸውን እቅድ እንዲያወጡና ከክፍሎቻቸው ሰራተኞች ጋር እንዲወያዩባቸው ማድረግ | በየደረጃው ያሉት የዩኒቨርሲቲው አካሎች የዩኒቨርሲቲውን ፕላን መሰረት በማድረግ እና በክሎቻቸው ከሚገኙ ሰራተኞች ጋር በመወያየት አመታዊ አቅዶቻቸውን አዘጋጅተዋል | | |
| | የሃብት አስተዳደር ስርዓት ማጠናከር | የውስጥ ቁጥጥር ስርአትን በማጠናከር የሃብት አስተዳደር ስርአቱን ለማሻሻል እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን በየደረጃው ለሚገኙ ሃላፊዎች ደግሞ ስለ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ስልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል። የ2005 የአንደኛ ሩብ አመት የፋይናንስ ኦዲት ተደርጎ ጥር 3/2005 ላይ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው አካላት በተገኙበት የመውጫ ኮንፈረንስ በማካሄድ መስተካከል ያለባቸው ጉድለቶች እንዲስተካከሉ ስምምነት ተደርሶበታል። ሪፖርቱ ለቦርድ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። የ2005 ሁለተኛው ሩብ አመት የውስጥ ኦዲት ተደርጎ በግኝቶቹ ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ተደርጎበታል። ከዚሁም በተጨማሪ ከፌደራል ዋና ኦዲተር በመጡ ባለሞያዎች እስከ ጥር 2005 ድረስ ያለው አሰራር ፕረሊሚናሪ ኦዲት ተደርጎ በቀረበው ሪፖርት ላይ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የመውጫ ኮንፈረንስ ተደርጎበታል። በፕረሊሚናሪ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ዋና ዋና ጉዳዮች ለቦርድ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። በቀረበው ሪፖርት መሰረት አስገላጊው መስተካከል ተደርጎባቸዋል። | | |
| | መመርያዎችን /የሰኔት ለጂስሌሽን፤ የቅጥርና ስኮላርሺፕ ማንዋሎች፤ የምርምርና ህብረተሰብ ኣገልግሎች መመርያ፤ የጥራትና ተገቢነት ማንዋሎች/ በማውጣትና በማፅደቅ ተግባራዊ ማድረግ ። | የዩኒቨርሲቲ ሌጂስሌሽን ዋናው አካል የሆነው የአካዳሚክ መመርያዎች በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ሊያገለግል በሚችል መልኩ እንዲስማማ ተደርጎ ስለተላከልን እየተጠቀምንበት እንገኛለን። ከዚሁ ውጭ በለጂስሌኝኑ መካተት ያለባቸው ነገሮች ተካተው ረቂቅ ለጂስሌኝኑ ተዘጋጅቶ መምህራን በየደረጃው እንዲወያዩበት ተደርጓል። የተደረጉ ውይይቶችን መሰረት በማድረግ በሰኔት ደረጃ ውይይት ተደርጎበታል። በዚሁም መሰረት የተሻሻለው ለጂስሌሽን ተበትኗል። ለጂስሌሽንን በተመለከተ አሁን የሚቀረው ስራ የመጨረሻው ድራፍት በሰኔት የማስፀደቅ ጉዳይ ይሆናል። የቅጥርና ስኮላርሺፕ ጊዜያዊ መመርያ በመጠቀም ላይ የምንገኝ ሲሆን ሌሎችን በተመለከተ በቀሪው ጊዜ የሚሰራ ይሆናል። | | |
| | BSCን መሰረት ያደረገ የዩኒቨርሲው የኣምስት ኣመት ስትራቴጂክ ፕላን ማዘጋጀት | የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂክ ፕላን ረቂቅ የሚያዘጋጅ ኮሜቴ ተሰይሞ አስፈላጊው ስልጠና እና ልምድ እንዲቀስም ተደርጎ ፕላኑን በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። ፕላኑ እስከ ደረጃ 6 ድረስ የተዘጋጀ ሲሆን በያንዳንዱ ክፍል ላይ ውይይት በማድረግ መዳበር ስለሚገባው የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተገኙበት ውይይት ተደርጎበት የማዳበርያ ሃሳብ ተሰጥቶበታል። በተሰጡት ሃሳቦች መሰረት የዳበረ ስትራቲክ ፕላን በቅርቡ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት የመጨረሻው ስእል የሚይዝ ይሆናል። | | |
| | የመረጃ አያያዝ ስርዓትን መዘርጋት | የተጠናከረ የመረጃ ስርአት ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ሶፍትዌር አመካኝነት መደገፍ እንደሚኖርበት ይታመናል። በዚሁም መሰረት በተለይ የተማሪዎች የመረጃ አያያዝ ስርአት አውቶሜት ለማድረግ ከሌሎች አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ በመሆን | በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኩል የተጠየቀው ዋጋ ከፍተኛ መሆን | ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመመካከር ሌሎች መፍትሄ ለመፈለግ ሃሳቦችን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተሰራው ሶፍትዌር በግዥ ወይም በሌላ መንገድ ለማግኘት ከፍተኛ ሙከራ የተደረገ ቢሆንም ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የጠየቀው ዋጋ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ሊሳካ አልቻለም። ሆኖም የተማሪዎች መረጃ ትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው EMIS በተባለው መሰረት ልከናል። | | አቅርበናል። በ2006 ከዋነኛ ስራዎች ውስጥ አንዱ ተደርጎ የሚያዝ ይሆናል |
| | የእቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | በየደረጃው የሚገኙ አካሎች በተደጋጋሚ እየተገናኙ የእቅድ አፈፃፀም ክትትል እንዲያደርጉ በእቅዱ በተቀመጠው መሰረት እየተሰራበት ይገኛል። የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል ቢያንስ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ እየተገናኙ ተግባራቸውን አከናውነዋል። የዩኒቨርስቲውን መምህራንና ሰራተኞች በሙሉ የሚያካትት በአመት ሶስት ጊዜ የዝግጅትና ግምገማ ስራዎች ተሰርተዋል። በባጀት አመቱ መጀመርያ ላይ በዩኒቨርሲቲው አመታዊ እቅድ ውይይት ተደርጎበታል። በአመቱ አጋማሽ ደግሞ የስድስት ወራት ግምገማ ተደርጓል። በአመቱ መጨረሻ (ማለት ሰኔ 29) ደግሞ የአመቱ ግምገማ ተደርጓል። | | |
| | ለሴቶች እና ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው አካላት ድጋፍ መስጠት | የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው በዋናነት ሴት ተማሪዎች እና እንዲሁም ወንድ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቁሳቁሶች /ደብተር እስክርቢቶ ሳሙና ሞዴስ/ ድጋፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ እንዲያመለክቱ ተደርጎ 115 (81 ሴት ተማሪዎች እና 34 ወንድ ተማሪዎች) ያህል ለዚሁ ተብሎ በተቋቋመ ኮሚቴ እንዲለዩ ተደርገው ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል። ከሚደረግላቸው የቁሳቁስ ድጋፍ በተጨማሪ በሰሚስተር 100 ብር ለያንዳንዱ የኢኮኖሚ ችግረኛ ተማሪዎች ተሰጥቷል። ከዚሁም ሌላ ከሴቶች ወጣቶችና ህፃናት ሚኒስቴር የተላከልን ገንዘብ በመጠቀም ለ30 ሴት ተማሪዎች (በ2004 የተመረጡ) በየወሩ ሁለት መቶ ብር ተሰጥቷቸዋል | | |
| | ከባለድርሻ አካላት ግንኙነት ማስፋትና ማጠናከር | ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረቶች እየተደረጉ ነው። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በጥሩ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ከከተማው አስተዳደር ጋር በመሆን የመስቀል በአል ማክበር እና ለከተማው የስፖርት ቡድን የተሰጠው የአንድ መቶ ሺ ብር ድጋፍ እንዲሁም ለከተማው ሆስፒታል የሚያገለግሉ በአራት ኮንተይነሮች የመጡ የህክምና ማቴርያሎች ለሆስፒታሉ መሰጠቱ የሚጠቀሱ ናቸው። | | |
| | የተጠናከረ የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መፍጠር | ዩኒቨርሲቲውን በማከናወን ላይ ያለውን ስራዎች ለማስተዋወቅ ፅሁፎችን በማዘጋጀትና ፕሮግራሞች በሬድዮና ቴሌቪዥን እንዲተላለፉ በማድረግ በጎ ስራዎች ተከናውነዋል። ከዚሁም በተጨማሪ አንድ መፅሄት ተዘጋጅቶ ለህትመት በቅቶ ተሰራጭቷል። | | |
| | በመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም አዋጆች ላይ ለዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች የግንዛቤ ት/ት መስጠት | ከመስከረም 11 – 13 በተደረገው የሶስት ቀናት ውይይት ከፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በመጡት እንግዶች እና በዩኒቨርሲቲው የሃይማኖት አክራሪነት ለማትና ዲሞክራሲ በሚል ርእስ ውይይት ተደርጎበታል። ከዚሁም በተጨማሪ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ፤ የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር፤ እና የካይዘን ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። እንዲሁም ከፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለ100 ተሳታፊዎች (70 ተማሪዎችና 30 ሰራተኞች) ስልጠና ተሰጥተቶ የሰላም ፎረም ተመስርቷል። | | |
| | አሳታፊ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ማጠናከር | የዩኒቨርሲቲ ሰራተኛ በየደረጃው እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሳተፍበት ስርአት ተዘርግቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። | | |
| | የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ስርዓት ማጎልበት | የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ፅ/ቤት ለማደራጀት ይቻል ዘንድ በአዲሱ መዋቅር የፀደቀ ሲሆን ለፅ/ቤቱ የሚሆን ሰራተኛ እስኪቀጠርለት ድረስ የህግ ፅ/ቤት ደርቦት እንዲሰራ እየተደረገ ይገኛል። ከስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመጡ ባለሞያዎች የስነምግባርና ፀረ ሙስና ንቅናቄ ስልጠና ለተማሪዎችና ሰራተኞች ተሰጥቷል። በዚሁም መሰረት ለሁሉም መምህራንና ሰራተኞች | | የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ባለሞያ/ዎች በ2006 የባጀት አመት ተቀረው ፅ/ቤቱ ራሱን ችሎ የሚዋቀር ይሆናል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ደግሞ ስልጠና ተሰጥቷል | | |
| ግብ 3. የመምህራን ልማት ማጠናከር | የመምህራን ልማት ፕላን የማውጣት አስፈላጊነት ታውቆ አስፈላጊ ዝግጅት ማድረግና ለፕላኑ መነሻ የሆኑ ነገሮችን ማዘጋጀት | የመምህራን ልማት ፕላን ያልተዘጋጀ ሲሆን ከስትራቴጂክ ፕላኑ በሚጣጣም መልኩ ለማዘጋጀት ይቻል ዘንድ ከፕላኑ ጋር አብሮ እየተሰራ ይገኛል፤ በስትራቴጂክ ፕላኑ እንዲካተት የሚደረግ ይሆናል። | | |
| | በመምህራን ልማት ዕቅዱ መሰረት መምህራንን ለከፍተኛ ት/ት መላክ | ዘንድሮ 27 መምህራን ለትምህርት ተልከዋል (አንዷ በራስዋ ፈቃድ አቋርጣለች)። | | |
| | በትምህርት ላይ የሚገኙትን መምህራን የት/ት ሁኔታ መከታተል | በትምህርት ላይ ከሚገኙት መምህራን ጋር በተለይ የኮምፒዩተር እገዛን በተመለከተ ክትትል እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን የኮምፒዩተር ግዥ ስለተከናወነ በትምህርት ላይ ላሉት መምህራን ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ተሰጥቷቸዋል። | | |
| | መምህራን በፔዳጎጂ እና በተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ(ለአዳዲስ መምህራን የኢንዳክሽን ስልጠና መስጠት) | ለአዲስ መምህራን በተለይና ለሁሉም መምህራን ባጠቃላይ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ በመጡ ባለሞያዎች የክፍል አያያዝ /Class room management/፤ የተማሪዎች ግምገማና ውጤት አሰጣጥ /Assessment and grading/፤ እንዲሁም ተማሪን ማእከል ያደረገ የማስተማር ዘዴ /Active teaching and learning/ በሚሉ ርእሶች የሶስት ቀናት (ጥቅምት 16–18/2005) ከ100 በላይ መምህራን በተገኙበት ስልጠና ተሰጥቷል። ከነዚህ ርእሶች በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው የወሲባዊ ጥቃት ፖሊሲ /Anti Sexual Harassment Policy/ ላይ በዩኒቨርሲቲው የስርአተ ፆታ ፅ/ቤት በኩል ስልጠና ተሰጥቷል። | | |
| ግብ 4. ብቁ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ስርአተ ትምህርቶች ማረጋገጥና መተግበር፤ | በተቀመጠው ዝርዝር መሰረት ኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎችን ማደራጀትና ካሪከለሞችን በመሰብሰብና ማስተካከል የሚያስፈልጋቸው ካሉ በማስተካከል ተዘጋጅተው በየደረጃው ውይይት ተደርጎባቸው እንዲፀድቁ ማድረግ | በ2004 የነበሩት የኮሌጆች ብዛት 4 ሲሆን በ2005 ወደ 6 እንዲያድጉ እና የትምህርት ክፍሎችን ቁጥር ከ13 ወደ 26 እንዲያድግ ተደርጓል። አዳዲሶቹ ትምህርት ክፍሎች ካሪከለም ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ በመቅሰም እንዲያዘጋጁ ተደርጓል። ሁሉም ትምህርት ክፍሎች ሞጁላራይዝድ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ እንዲተገብሩ ተደርጓል። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ተከታታይ ምዘና /Continuous Assessment/ እና መስፈርት ወይም ክራይተርያ መሰረት ያደረገ /Criterion Referenced/ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት መከተል። ለአፈፃፀምም ይረዳ ዘንድ አስፈላጊ የአፈፃፀም መመርያዎችን ማዘጋጀት፤ መግባባት መድረስ፤ ማስፈፀምና አፈፃፀሙን መከታተል | የተከታታይ ምዘና እና ቋሚ መስፈርት ያደረገው የነጥብ አሰጣጥ ስርአት ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል። ለአፈፃፀሙ ይረዳ ዘንድ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እና በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ ክትትል በቀጣይነት መልኩ ተደርጎበታል። | | |
| | በከተማው ከሚገኘው ሆስፒታል ጋር በመነጋገር የህክምና ኮሌጅ በማጠናከር ተማሪዎችን ማስተናገድና የጋራ ቅጥር በተመለከተ ስምምነት መድረስና ማስፈፀም | በከተማው ከሚገኘው ሆስፒታል ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን በማድረግ ጥሩ የትብብር መንፈስ ተፈጥሯል። በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሚገኙ የሚድ ዋይፈሪ አስተማሪዎች በሆስፒታሉም ለአንድ ሰሚስተር እንዲሰሩ ተደርጓል። ከዚሁም አልፎ ሆስፒታሉ ያለውን ከፍተኛ የቁሳቁስ ችግር ለመፍታት በስዊድን አገር ከሚገኘው Human Bridge ከተባለው ድርጅት ጋር በመነጋገርና የስምምነት ሰነድ /MoU/ በመፈራረም የመጓጓዣ ወጪ በዩኒቨርሲቲ እንዲሸፈን ተደርጎ አራት ኮንተይነሮች ደርሰው ለሆስፒታሉ እንዲደርሰው ተደርጓል። | | |
| | የModularization/Preparation of consecutive modules/ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ | በዩኒቨርሲቲው በአመቱ ከተሰሩት አበይት ተግባራት አንዱ የሞዱላራይዝድ የትምህርት አሰጣጥ ስርአት ማስፈፀም ነው። በዚሁም መሰረት ከ2004 ክረምት ጀምሮ ከፍተኛ ዝግጅት /ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመገናኘትና ሞዱላራይዜኝኑን በማስማማት/ በማድረግ ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ ገብተናል። | | |
| ግብ 5. የ70 በ 30 ቀመር ላይ የተመሰረተ ሃገራዊ የተሳትፎ መጠንን እውን ማድረግ፤ | የተማሪዎች ስብጥር ወደዩኒቨርሲቲው በየባንዱ የሚመደቡ ተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ቢሆንም አመዳደቡ 70 በ 30 ቀመር ላይ መሰረት ያደረገ እንደሚሆን ስለሚጠበቅ ይሄንን መሰረት ያደረገ የመምህራን ቅጥር ለማስፈፀም ጥረት ማድረግ | የ70፤30 ቀመር በማድረግ የኮሌጆችና የትምህርት ክፍሎች መስፋፋት የተደረገ ሲሆን ጥሩ ውጤትም ተገኝቶበታል። በዚሁም መሰረት 72% የሚሆኑት ተማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስኮች በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን 28% ደግሞ በማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት መስኮች ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 6. የከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ፤ የተማሪዎች ተሳትፎ ማረጋገጥ | የሴት ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተቻለ መጠን ቅድሚያ በመስጠት በመረጡዋቸው የትምህርት መስኮች እንዲመደቡ ማድረግ፤ | በፕላኑ በተቀመጠው መሰረት ተማሪዎች ወደየትምህርት ክፍሉ በሚመደቡበት ጊዜ 25% የሚሆኑት ቦታዎች ለሴቶች ብቻ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ | | |
| | የሴት ተማሪዎችን፤ አካል ጉዳተኞችን እና ከአዳጊ ክልልሎች የመጡ ተማሪዎችን ያማከለ የቱቶርያል እና የማጠናከርያ /ሬሜድያል/ ድጋፍ ማድረግ፤ የሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት እንዲማሩ የሚያስችለውን አካሄድ መከተል | የቱቶርያል ስራዎች በየትምህርት ክፍሉ የሚከናወኑ ሲሆን የተማሪዎችን ውጤት መሰረት ባደረገ መልኩ የማጠናከርያ ድጋፍ የማድረጉ ጉዳይም ከተከታታይ ምዘናው ጋር በተያያዘ መልኩ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ከዚሁ አልፎ የተማሪዎች የአንደኛ ሰሚስተር ውጤት ከታየ በኋላ የድህረ ማጠናከርያ (ድህረ ሬሜድያል) ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ረሜድያል ተሰጥቶ ተማሪዎች እንደገና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ በዚህም በርካታ ተማሪዎች ውጤታቸውን አሻሽለዋል፤ 140 የሚሆኑት ደግሞ ከመባረር ድነዋል፡፡ | | |
| | የተማሪዎች ካውንስል እንዲጠናከር ድጋፍ ማድረግ፤ የተማሪ ክበቦች እንዲመሰረቱ ድጋፍ ማድረግ | የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ካውንስል በየደረጃው ጠንካራ ተሳትፎ የሚያደርግ ሲሆን ካውንስሉ ተግባራቱን እንዲያከናውን በዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ የተማሪዎች የፓሊስ ክበብ፤ የአረንጓዴ ክበብ፤ የስነ ጥበብ ክበብ፤ የሰላምና መቻቻል ክበብ እና የፀረ ሙስና ክበብ ተመስረተው በጥሩ እየሰሩ ይገኛል | | |
| | የካውንስል /የተማሪ ተወካዩች/ በሰኔት፤ በኮሌጅ ካውንስል፤ በትምህርት ክፍል ካውንስል፤ በምግብና እንዲሳተፉ ማድረግ | የተማሪ ተወካዮች በተጠቀሱት እርከኖች በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ | | |
| | የተማሪ የክፍል ተወካዩች ማስመረጥ ከትምህርት ክፍል ሃላፊ ጋር ተከታታይ ግንኙነቶችን መፍጠር፤ በሰሚስተር አንድ ጊዜ በኮሌጅ ደረጃ ከክፍል ተወካዮች ጋር ግምገማ ማድረግ | ከየክፍሉ ሁለት ሁለት ተማሪዎች (ቢያንስ አንዱ ሴት እንድትሆን በማድረግ) በክፍል ተወካይነት እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ ተወካዮቹ ከየትምህርት ክፍሎቻቸው ጋር ክትትል የሚያደርጉ ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃም ሁሉም ተወካዮች በተገኙበት ሁለት የውይይት መድረክ (አንዱ በአንደኛው ሰሚስተር ሌላኛው በሁለተኛው ሰሚስተር) ተደርጎ ግምገማ ተካሂዷል፡፡ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ተማሪዎች እርስ በርስ የሚተጋገዙበት የአንድ ለአምስት ኔትወርኪንግ /Cooperative Learning/ እንዲፈጠር ማድረግና አፈፃፀሙን መከታተል | 645 የአንድ ለአምስት የተማሪዎች መረቦች በየትምህርት ክፍሉ እንዲደራጁ ተደርገዋል፤ ከ146 የመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች የአንድ ለአምስት መረቦች ደግሞ ተመስረተዋል። አፈፃፀሙ በተመለከተም የተማሪዎች መረቦች የተሻለ አፈፃፀም የነበራቸው ሲሆን በ2006 የትምህርት ዘመን ደግሞ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። | | |
| ግብ 7. ለኢንዱስትሪ ልማት አስተዋፅኦ የሚያደርግ ተቋሚዊ አቅምን ማረጋገጥ፤ | በአከባቢው እና በክልሉ ከሚገኙ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ትስስር ለመፍጠር የመነሻ ጥናቶችን ማድረግና መጀመር | ከኤፈርት ድርጅቶች ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል አንድ የመነሻ ፅሁፍ ተዘጋጅቶ በከተማው ከሚገኘው የመድሃኒት ፋብሪካ ጋር ግንኙነት ተደርጎበታል። ከተመሳሳይ ድርጅቶችና ከኤፈርትም ጋር በቀጣይ አመታት ተጠናክሮ መሄድ የሚኖርበት ይሆናል። | | |
| | ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን ለመደገፍና ለማጠናከር ዝግጅቶችን ማድረግ | በከተማው ውስጥ የሚገኙ 53 ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በዩኒቨርሲቲ ግንባታ ስራ ውስጥ ስለሚሳተፉ በርካታ ወጣቶች የስራ እድል አግኝተዋል። ከዚሁም በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው በሚያከናውናቸው ግዥዎችና በሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንዲሳተፉ (በውድድር) እየተደረገ ይገኛል። በዚሁም መሰረት ለተማሪዎች የሚቀርበው ስጋ እና እንቁላል በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በመቅረብ ላይ የሚገኝ ሲሆን የፅዳት ስራን ወደ ውጭ ለማውጣት በተያዘው ፕላን መሰረት አንድ ማህበር ውድድሩን አሸንፎ ስራውን እየሰራ ይገኛል። ከዚሁም በተጨማሪ ሸሮ እና በርበሬ በማህበር ቀርቦልናል። በዚሁም መሰረት ለበርካታ ማህበራት የስራ እድል ተፈጥሯል። | | |
| | የማህበረሰብ አገልግሎች ስራዎችን መለየትና በተወሰኑት ላይ የተቻሉትን ድጋፎች ማድረግ | ከከተማው አስተዳደር ጋር በመተባበር የከተማውን እግር ኳስ ክበብ ለመደገፍ የተሰጠው ገንዘብ (ብር አንድ መቶ ሺ) እና የከተማው ሆስፒታል በህክምና እቃዎች ለመደገፍ የተደረገው ጥረት ዩኒቨርሲቲው በማድረገ ላይ የሚገኘውን የማህበረሰብ አገልግሎት የሚያመላክቱ ናቸው። ከዚሁም በተጨማሪ መጠቀስ ያለበት በትምህርት ጥራት ላይ ዩኒቨርሲቲው እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ሲሆን ከ300 በላይ ለሆኑ መምህራንና የትምህርት | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ባለሞያዎች የሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል። | | |
| ግብ 8. ሃገራዊ ፖሊሲንና ፋይዳን ያማከለ ተቋሚዊ የጥናትና ምርምር አቅምን መገንባት፤ | ለምርምር ስራዎች አመቺ የሆነ አደረጃጀት መፍጠር | መምህራን ከአጠቃላይ ስራቸው ውስጥ ቢያንስ 25% የሚሆነውን ለምርምር ስራ ማዋል እንዳለባቸው ይታወቃል። በዚሁም መሰረት በ2005 የትምህርት ዘመን 71 የምርምር ፕሮፖዛሎች በመምህራን የቀረቡ ሲሆን ፕሮፖዛሎቹ በኮሌጅ ደረጃ እንዲወዳደሩ ተደርገው በጥንካሬ ደረጃቸው እንዲለዩ ተደርጓል። በመጨረሻም 23 ፕሮፖዛሎች ተመርጠው 1.6 ሚልዮን ባጀት ተመድቦላቸው በመሰራት ላይ ይገኛሉ። | | |
| | የምርምር ፈንድ አመዳደብ እና የአጠቃቀም ስርዓት ማበጀት እና መተግበር | የምርምር ባጀት ፀድቆ የተመደበልን ሲሆን በዚሁም መሰረት ለባጀት አመዳደብ ያመች ዘንድ መጀመርያ በየኮሌጁ ፕሮፖዛሉች እንዲወዳደሩ እና የተሰጣቸውን ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተዋቀረ ኮሚቴ የመጨረሻው መረጣና ባጀት ምደባ ተደርጓል። | | |
| | ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው የምርምር መስኮችን መለየት እና ደረጃ ማውጣት | የምርምር ፕሮፖዛሎች በሚመረጡበት ጊዜ ያላቸው ሃገራዊ ፋይዳ (ማለትም የአገሪቱን ፖሊሲና ስትራቴጂ ለማሳካት ያላቸው ፋይዳ) እንደ መምረጫ ክራይቴርያ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። በክልሉ በመተግበር ላይ ያለውን የተቀናጀ ፓኬጅ ፕሮግራም ያስገኘው ወጤት በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው ምርምር በማድረግ ላይ ይገኛል። | | |
| | የተለያዩ workshop፣ seminar፣ symposiums እና የመሳሰሉ ማዘጋጀት እና መተግበር | ዩኒቨርሲቲው የመጀመርያውን ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ በበለስ ላይ ህዳር 22/2001 አካሂዷል። | | |
| ግብ 9. የዩኒቨርሲቲውን ገቢ ምንጮች በብዛትና በመጠን ማጠንከር። | የገቢ ምንጮች ሊሆኑ የሚችሉ መስኮችን መለየትና ዝግጅቶችንና እንቅስቃሴዎችን ማድረግ | ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ የውስጥ ገቢ ማጠናከር ይጠበቅበታል። በዚሁም መሰረት አንዳንድ ጅምር ስራዎች እየተሰሩ ነው። በዋናነት እየተሰራ የሚገኘው የማታ ተከታታይ ትምህርት ነው። በዚሁም አማካኝነት በፕሮግራሙ የሚሳተፉ መምህራን ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። ከዚሁም በተጨማሪ ከክልሉ የፕላንና ፋይናስ ቢሮ ጋር በመተባበር የአንድ ሚልዮን ብር ጥናት በማድረግ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ላይ ይገኛል፤ ከዚሁም ዩኒቨርሲቲው ገቢ የሚያገኝ ይሆናል። | | |
| | የማታና የክረምት ትምህርቶች፤ | በማታው ትምህርት 295 ተማሪዎች (በአራት የትምህርት ክፍሎች) ያሉን ሲሆን ከሚቀጥለው ክረምት ጀምሮ የክረምት ትምህርት ለመጀመር ዝግጅቶች በመደረግ ላይ ናቸው | | |
| | የዎርክሾፐ ስራዎች፤ የማማከር ስራዎች፤ | በዚህ በኩል የተሰሩ ስራዎች የሉም | ዎርክሾፖች ገና ስራ አልጀመሩም | |
| | የምርምርና የትብብር ፕሮጀክቶችን መቅረፅ፤ | አሜሪካን አገር ከሚገኙ ከቴክሳስ ቴክ ዩኒቨርሲቲ እና ከኬንታኪ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ጋር የስምምነት ሰነድ ተፈራርመናል። | | |
| ግብ 10. የኢንተርኔትና ኮሙኒኬሽነ ስራዎችን ማስፋትና ማጠናከር | የኢንተርኔት አገልግሎት በሲዲኤምኤ እና ኢቪዶ አመካኝነት ከትምህርት ክፍል ሃላፊ ጀምሮ ለሁሉም ክፍሎች ማዳረስ። | በየደረጃው የሚገኙ ሃላፊዎች በሲዲኤም ኤ እየተጠቀሙ ሲሆን ለመላው የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰት (በተለይም ለመምህራን) አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ የኮምፐዩተር ላብ አለን። የኮምፕዩተር ላቡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢቪዶ ሲሰራ የነበረ ሲሆን የፋይበር ኦፕቲክ መስመር ወደ ዩኒቨርሲቲው በመዘርጋቱ ምክናያት በዚሁ መስመር በመጠቀም ላይ እንገኛለን። | | |
| | ቪድዮ ኮንፈረንስ እና ሌሎች ክፍሎች ማደራጀት | ይህ ስራ ብቃት ያለው የኔትወርክ ዝርጋታ የሚጠይቅ ስለነበር አልተከናወነም | የውስጥ ለውስጥ ኔትወርክ ዝርጋታ ይፈልጋል | ከኦርቢስ ኢንተርናሽናል የገመድ አልባ ኔትወርክ እቃዎች ለመግዛት ያስችለን ዘንድ ለኮሙኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ፈቃድ እንዲሰጠን ጥታቄ አቅርበን ተፈቅዶልን ግዥ ተከናውኗል |
| | የe-learning ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ | ይህ ስራ ብቃት ያለው የኔትወርክ ዝርጋታ የሚጠይቅ ስለነበር አልተከናወነም። ሆኖም ዲጂታል ላይብረሪ በአንድ ክፍል በ30 ኮምፕዩተሮች ተጀምሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። | የውስጥ ለውስጥ ኔትወርክ ዝርጋታ እና ለስራው የሚሆን ሶፍትዌር ያስፈልጋል | የዲጂታል ላይብረሪ ስራ በ2006 ተስፋፍቶና ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል |
| | የዩኒቨርሲቲው ድረ ገጽ ማጠናከር | የዩኒቨርሲቲው ድረ ገፅ እንደ አዲስ ተጠናክሮ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እና ይዘቱን ማበልጸግ | አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። | | |
| | የዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች አውቶሜት ማድረግ /በተለይም የረጂስትራር አሰራርን ይመለከታል/ | ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በመተባበር ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ይገኛል የተባለው ሶፍትዌር በዋጋ በውድነት ምክንያት ሊገኝ አልቻለም | | |
| | የፋይበር ኦፕቲክስ ተከላ ስራ ማከናወን | ወደ ግቢው ውስጥ የፋይበር ኦፕቲክ መስመር አስገብተናል። የግቢ ኔትወርክ ዝርጋታ ለማድረግ የሚያስችሉን ማቴርያሎች ስለተገዙ ወደየቢሮው የሚደረግ የኔትወርክ ዝርጋታ በ2006 የሚከናወን ይሆናል። | | |
| | የኮምፒዩተሮች፤ ፕሪንተሮችና የኔትዎርክና ተጓዳኝ እቃዎች የጥገና ስርዓትን ማጠናከር | በአዲሱ መዋቅር መሰረት ይሄንን ስራ ሊሰራ የሚችል የICT ማእከል እንዲፈጠርና ሰው እንዲመደብለት ተደርጓል | | |

4. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በ2005 የበጀት አመት በርከት ያሉ ችግሮች ያጋጠሙ ሲሆን በዋናነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ሲሆን ችግሮችን ለመፍታት ወይም ለመቀነስ የተወሰዱት መፍትሂዎችም አብረው ቀርበዋል።

1. የሴፕቲክ ታንክ ሞልቶ መፍሰስ

የዩኒቨርሲቲው ፍሳሽ የሚጠራቀምበት አንድ ሴፕቲክ ታንክ ያለ ቢሆንም ሴፕቲክ ታንኩ ሞልቶ መፍሰስ በመጀመሩ በአከባቢው ላይ ችግር እየፈጠረ ይገኛል። ዘላቂ መፍትሂ የሚሆነው የትሪትመንት ፕላንት መስራት ሲሆን ፕላንቱ እስኪሰራ ድረስ ሁለተኛ የሴፕቲክ ታንክ በማሰራት ላይ እንገኛለን። አዲሱ ሴፕቲክ ታንክ ሲጠናቀቅም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መሙላቱ አይቀሬ ነው። የትሪትመንት ፕላንት ዲዛይን እና የዋጋ ግምት ተጠናቆ የግቢው የመሰረተ ልማት ግንባታውን በመስራት ላይ የሚገኝ ስራ ተቋራጭ የትሪትመንት ግንባታውንም እንዲሰራ ስምምነት ላይ ስለተደረሰበት ስራውን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል። ለትሪትመንት ፕላንት ስራ ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ ሃያ ሄክታር መሬት እንዲሰጠን ለጋንታ አፈሹም ወረዳ አስተዳደር ጠይቀን የተፈቀደልን ሲሆን የካሳ ክፍያው በተመለከተ የግመታ ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ ናቸው። ከዚሁ ጎን ለጎንም የመጣጭ መኪና አቅርቦት ይኖር ዘንድ ጥያቄውን ለትምህርት ሚኒስቴር ቀደም ብለን ያቀረብን ሲሆን ግዥው ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር አብሮ ይከናወናል በሚል በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

2. በተማሪዎች ዶርሚተሪ ያሉት ሽንት ቤቶች የሚያጋጥሙ ችግሮች

በ2004 አምስት የዶርሚተሪ ብሎኮች የነበሩን ሲሆን በ2005 ደግሞ አስራ ሶስት ተጨማሪ ዶርሚተሪዎች ተሰጥተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በ2004 ስንጠቀምባቸው የነበሩት ዶርሚተሪዎች ውስጥ ያሉት ሽንት ቤቶች የአሰራር ችግር ስለነበረባቸው ባለፈው ክረምት አንዳንድ መስተካከል እንዲደረጉላቸው ተደርገዋል። በአስራ ሶስቱ ዶርሚተሪዎች ደግሞ ገና ግንባታዎቹ በመካሄድ ላይ እያሉ በመጀመያዎቹ ዶርሚተሪዎች ያጋጠሙ ችግሮች እንዲቃለሉ በሚል እሳቤ መሻሻል ስለተደረገላቸው (ፍሳሹ በአንድ ራይዘር ከሚወርድ ይልቅ በሁለት ራይዘር እንዲፈስ ተደርጎ ተስተካክሏል) አገልግሎቱ የተሻለ ቢሆንም አሁንም ችግሩ ሙሉ ለሙሉ የተወገደ አይደለም። ችግሮቹ በአንድ በኩል የአሰራር ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የአጠቃቀም ናቸው።

እስሎፕ ሳይጠብቁ መስራት፤ የሽንት ቤት ቱቦዎች በደንብ ያልተገጠሙ መሆን፤ እና የፍሳሽ መንገዶች መዘጋት በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በርከት ባሉ ህንፃዎች ውሃ ወደ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ፍሎር ሊወጣልን አልቻለም። በአመቱ መጀመርያ አከባቢ ከአንድ ጉድጓድ በሚሳብ ውሃ ብቻ እንጠቀም ስለነበረ መጠኑ እንዳይቀንስ ወይም ብልሽት እንዳያጋጥም ስጋት የነበረን ቢሆንም አስፈላጊው ነገር ተሟልቶ 15 ሊትር በሰከንድ ከሚያመነጭ ሁለተኛ ጉድጓድ መጠቀም ስለጀመርን ስጋቱ ሊቀረፍ ችሏል። ሆኖም ከሪዘርቫየሩ ወደ ክፍሎች የሚሰራጨው ውሃ በዲዛይኑ መሰረት ሳይሆን በጊዜያዊነት በተሰራ መስመር (የእሳት ማጥፊያ መስመር) ስለሆነ በበርካታ ህንፃዎች ወደ ሁለተኛና ሶስተኛ ወለሎች ሊደርስ አልቻለም። ለዚሁ ችግር በስራ ተቋራጩ የተሰጠው ምክንያት በዲዛይኑ የተቀመጠው ባለ 400 ቱቦ በአገር ውስጥ የሌለ መሆኑ ነው። አሁን ተፈላጊው ቱቦ በአገር ውስጥ መመረት ስለጀመረ አስፈላጊው ቱቦዎች ተገዝተው በዲዛይኑ መሰረት የመግጠም ስራ የተጀመረ ሲሆን ችግሩ በቅርቡ ይፈታል ተብሎ ተስፋ እየተደረገ ነው። ሌላው እስካሁን መቃለል ያልቻለው ችግር የሽንት ቤት አጠቃቀም ጉዳይ ሲሆን ፀጉር እና ሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች ሽንት ቤቶች ላይ በተማሪዎች እየተጨመሩ የፍሳሽ መስመሮችን መዝጋታቸው ነው (እነዚህ በሴቶች ዶርሚተሪዎች ይበረክታሉ)። በፕሮክተሮችና የተማሪ የወለል (ፍሎር) እና የብሎክ ተወካዮች ገለፃና ክትትል የሚደረግ ቢሆንም ችግሩ በወሳኝ መልኩ ሊፈታ ስላልቻለ ተጨማሪ ጥረት የሚጠይቅ ሆኗል።

3. አሸናፊ አቅሪቢዎች ያሸነፉዋቸውን እቃዎች በወቅቱ አለማቅረብ

ጨረታ ወጥቶ ያሸነፉ አቅራቢዎች ውል ካሰሩ በኋላ በወቅቱ እቃዎቹን ሊያቀርቡልን ያለመቻል ሌላው ያጋጠመው ችግር ነው። እንደምክንያት የሚያቀርቡት ከውጭ ምንዛሬ መዘግየት ጋር እና ከውጭ የሚመጡት እቃዎች በወቅቱ አለመድረስ ጋር የተያያዙ ናቸው።

**4. ላቦራተሪዎችና ዎርክሾፖች ተደራጅተው ስራ አለመጀመራቸው**

በርካታ የዎርክሾፕ እቃዎች ቀደም ብሎ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በወጣው ጨረታ መሰረት የቀረቡልን ሲሆን አብዛኛዎቹ አቅራቢዎቹ መሳርያዎቹን ተተክለው ስልጠና ተሰጥቶባቸው ጥቅም ላይ ይገኛሉ። የሲቪል ኢንጂነሪንግ የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ እና የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ እቃዎች በተማሏ ደረጃም ባይሆን ለተማሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን ሌሎች ግን አገልግሎት ላይ መዋል ባለመጀመራቸው እንደ መፍትሄ የወሰድነው ተማሪዎቹን ወደ መቐለ እና አክሱም ዩኒቨርሲቲዎች በመላክ አስፈላጊው የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ ነው። የላቦራቶሪ ትምህርት በተመለከተም በርካታ የላቦራቶሪ ህንፃዎች የተሰሩ ቢሆንም አስፈላጊ ማቴርያሎች ግን ገና የተሟሉላቸው አይደሉም። በዚሁም ምክንያት ለተማሪዎቻችን የተሟላ የላቦራቶሪ አገልግሎቶች በግቢው ውስጥ መስጠት ገና አልጀመርንም። ሆኖም በሁለተኛ ሰሚስተር ለባዮሎጂ እና ኬሚስትሪ ተማሪዎች አራት የላቦራቶሪ ክፍሎችን በማዘጋጀት የላቦራቶሪ አገልግሎት በመስጠት መሰጠት ተጀምሯል። ላቦራቶሪዎችን ያደራጀነው መቐለ ዩኒቨርሲቲ ዓይደር ካምፓስ ይጠቀምባቸው የነበረው የላቦራቶሪ ጠረጴዛዎችን (ለራሳቸው በሌላ ስለተኩዋቸው እነሱ ይጠቀሙበት የነበረውን በነፃ ስለሰጡን) በመጠቀም እና ሌሎች መሟላት ያለባቸውን የውሃና የኤሌክትሪክ መስመሮችን በመዘርጋት ነው። የላቦራቶሪ ክፍሎችን ከማደራጀት በተጨማሪ የላቦራቶሪ ኬሚካሎችና ማቴርያሎች በለቀማ ተገዝተው የተዘጋጁ በመሆኑ ለሁለተኛ ሰሚስተር የሚሆን አገልግሎት ተሰጥቶባቸዋል። ሆኖም የፊዚክስ፤ የግብርና እና የህክምና ላቦራቶሪዎች ገና ስላልተዘጋጁ ወደ መቐለ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በመላክ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርገዋል።

**5. የተሟላ የክሊኒክ አገልግሎት ያልተሰጠ መሆኑ**

ዩኒቨርሲቲው ጊዚያዊ ክሊኒክ አቋቁሞ ለተማሪዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከክሊኒኩ ችሎታ በላይ የሆኑት ችግሮች ደግሞ በከተማው ከሚገኘው ሆስፒታል ጋር ውል በመፈራረም ተማሪዎች አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል። ክሊኒኩን በተመለከተ ያጋጠመው ችግር መድሃኒት ለመግዛት ደረጃውን የጠበቀ የክሊኒክ ህንፃና አደረጃጀት ስለሚጠይቅ ፈቃድ ማግኘት አልተቻለም። ይህ የሆነበት ምክንያት ለክሊኒክነት ተብሎ እየተሰራ ያለው ህንፃ ስላልደረሰ ሲሆን ህንፃው በቅረቡ ይደርሳል ተብሎ እየተጠበቀ ስለሆነ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመድሃኒት ግዥ ለ2006 የሚፈቀድልን ይሆናል።

**6. የአንድ ለአምስት ኔትወርኮች በሚፈለገው መልኩ የተጠናከሩ አለመሆን**

በሪፖርቱ እንደተቀመጠው 791 የተማረዎችና የሰራተኞች ኔትወርኮች የተቋቋሙ ቢሆንም ጥንካሬያቸው ግን የሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም። የተማሪዎች ኔትወርኮች ከሌሎቹ ሻል ያለ እንቅስቃሴ የሚታይባቸው ቢሆንም እነሱም ቢሆን በቀጣይነት የድጋፍና ክትትል የሚሹ ናቸው። ስለዚህ የትምህርት ሰራዊት ከመገንባት አኳያ ሲታይ የተማሪና የሰራተኛ ኔትወርኮች በ2006 የባጀት ዘመንም የዩኒቨርሲቲው የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።